# ጥናት አንድ ዮሐንስ 1፡1-18 ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ማቴዎስና ሉቃስ በሥጋ የተወለደበትን ታሪክ በመናገር፣ ማርቆስ ደግሞ ኢየሱስ ወደ አገልግሎት የተሰማራበትን ሁኔታ በመተረክ የጀመሩ ሲሆን ዮሐንስ ግን የኢየሱስን ዘለዓለማዊነትና ከጥንትም የነበረ መሆኑን በመተረክ ይጀምራል፡፡ ‹‹በመጀመሪያ›› በማለት የሚጀምረው ሌላ መጽሐፍ ዘፍጥረት ነው፡፡
2. በዚህ ክፍል ኢየሱስን የሚያቀርብልን እንደ ፈጣሪ ሲሆን፤ በእርሱ ያልተፈጠረ ደግሞ ምንም ነገር እንደሌለ ነው የሚነግረን፡፡
3. ዮሐንስ የእግዚአብሄር መልዕክተኛ ሲሆን፤ ተልዕኮ ደግሞ ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ እንዲያምኑ ስለ ብርሃን ምስክር ሆኖ መቆም ነበረ፡፡ ዮሐንስ ሰዎች በኢየሱስ እንዲያምኑ በእግዚአብሄር የተላከ እንደነበረ እኛም ለዚሁ ተልዕኮ በኢየሱስ እንደተላክን እንመለከታለን፡፡
4. ብዙ ጊዜ የተጠቀሰው ቃል ብርሃን የሚል ሲሆን፤ ሰባት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ቁ9 ኢየሱስ ለሰው ሁሉ ብርሃን ሰጪ እንደሆነና እርሱ ደግሞ እውነተኛው ብርሃን እንደሆነ ይነግረናል፡፡
5. እነዚህ የሚላቸው ሰዎች በቁ12 ላይ ኢየሱስን የተቀበሉና በስሙ ያመኑትን ሰዎች ነው፡፡ ይህ ቁጥር  ሰዎች ከስጋና ከደም ከመወለድ አልፈው፤ ኢየሱስን በማመን ለሁለተኛ ጊዜ ከእግዚአብሄር መወለድን ስለማግኘት የሚናገር ሲሆን፤ በዮሐ 3፡3 ላይም ኢየሱስ የተናገረው ይኸንኑ እውነት ‹‹ዳግም መወለድ›› በማለት ሲያስተምረው እንዳስተማረው እንረዳለን፡፡
6. በቁ1-2 ላይ ዮሐንስ ማረጋገጥ የፈለገው ቃል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ እግዚአብሄር እንደሆነ፤ ከእግዚአብሄር ጋራ እንደነበረ ሲሆን፤ በቁ14 ላይ ደግሞ ማረጋገጥ የፈለገው ይህ ቃል አምላክ ብቻ ሳይሆን የሰውን ስጋ ለብሶ ሰው እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ክብሩን ያየው ጴጥሮስም በ2ኛ ጴጥ 1፡16-18 እንደሚጠቅሰው ማቴ 17፡1-9 አብረውት የሄዱት ሶስቱ ደቀመዛሙርት በተራራው ላይ በነበሩበት ወቅት የተመለከቱትን ሁኔታ ነው የሚናገረው፡፡
7. በብሉይ ኪዳን ጸጋ አልነበረም ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ መስዋዕት እግዚአብሄር ሰዎች እንዳይጠፉ የከፈተው መንገድ ነበረ፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን በዚያው ቁ17 ላይ እንደምናነበው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የመጣው ጸጋና እውነት ሙላት ያለው፣ የተትረፈረፈና ለሁሉም የሚበቃ ነው፡፡ ይህ አነጋገር የሚያመለክተን የእግዚአብሄር ጸጋ በሰዎች ህይወት ውስጥ ምን ያህል የበዛና የተትረፈረፈ እንደሆነ ያሳየናል፡፡
8. ሙብት የተሰጣቸው ሰዎች የተቀበሉትና በስሙ ያመኑት ሰዎች ሲሆኑ፤ የተሰጣቸውም ሙብት ‹‹የእግዚአብሄር ልጆች›› መባል ነው፡፡

# ጥናት ሁለት ዮሐንስ 1፡19-34 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጥያቄ የነበራቸው ሰዎች አይሁዶች ሲሆኑ፤ ጥያቄያቸውም የዮሐንስ ማንነት ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ እንዲጠይቁ የተላኩት ሰዎች ካህናትና ሌዋውያን ነበሩ፡፡
2. አንዱ አስረግጦ የተናገረው እውነት፤ እርሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ነው፡፡ በቁ20-23 የተጠየቃቸው ሶስቱ ተጨማሪ ጥያቄዎች፡ ኤልያስ ነህ? ነብዩ ነህ? ታዲያ እነዚህን ሁሉ ካልሆንክ አንተ ማን ነህ? ወይም ስለራስህ ምን ትላለህ? የሚሉት ናቸው፡፡
3. የዮሐንስ መልስ፡ ኤልያስም አይደለሁም፣ ነብይም አይደለሁም፣ ነገር ግን ‹‹ለጌታ መንገድ አቅኑለት እያለ በምድረበዳ የሚጮህ ድምጽ እኔ ነኝ፡፡›› በማለት ነው የመለሰው፡፡ እርሱ ስለራሱ ነብይ እንዳልሆነ ሲያረጋግጥላቸው፤ ኢየሱስ ግን ስለ እርሱ ሲመሰክር ከነብይም የበለጠ ነው ይለዋል፡፡
4. በዚህ ክፍል የቀረበለት ጥያቄ፡ ክርስቶስ፣ ኤልያስ ወይም ነብዩ ካልሆንክ ለምን ታጠምቃለህ? የሚል ሲሆን፤ ለጥያቄውም መሰረት የሆነው ነገር ዮሐንስ ለመጀመሪያው ጥያቄ የሰጠው መልስ ነበረ፡፡
5. የዮሐንስ መልስ፡ እኔ የማጠምቀው በውሃ ነው፤ ነገር ግን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል የሚል ነው፡፡ ኢየሱስ እነርሱ የማያውቁት እንደሆነ፣ በመካከላቸው እንዳለ፣ ከዮሐንስ በኋላ እንደሚመጣ፣ ዮሐንስ የጫማውን ማሰሪያ እንኳን ለመፍታት አይበቃም፡፡ ይህ ሁሉ የተካሄደው በዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ ነበረ፡፡
6. ያስተዋወቀው ‹‹የዓለምን ሃጥያት የሚያስወግድ የእግዚአብሄር በግ››በማለት ነበረ፡፡ ይህ በግ የሚለው ለሃጥያታችን መስዋዕት መሆኑን ለማመልከት ሲሆን፣ በራዕይ ውስጥ እንደ አንበሳ መጠቀሱ ደግሞ ድል አድራጊነቱንና አሸናፊነቱን ለመግለጽ የተሰጠው ስም ነው፡፡
7. ዮሐንስ ይህንን ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ በ1፡1 ላይ የተነገረውን የኢየሱስን ዘላለማዊነት ለመጠቆም ሳይሆን እንደማይቀር አምናለሁ፡፡
8. ‹‹አየሁ›› ‹‹የምታየው›› ‹‹አይቻለሁ›› በማለት ሶስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ የዮሐንስ ውሳኔ፡ ኢየሱስን ስላየሁትና ስላወቅሁት እርሱ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እመሰክራለሁ የሚል ነው፡፡

# ጥናት ሶስት ዮሐንስ 1፡35-51 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዮሐንስ ከሁለቱ ደቀመዛሙርቱ ጋራ ነበረ፡፡ ሁለቱም ሰዎች ኢየሱስን ለመከተል ሲሄዱ ይታያል፤ ለዚህም ምክንያት የሆነው ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የተናገረው ‹‹እነሆ! የእግዚአብሄር በግ›› ነገር ነበረ፡፡
2. በዮሐ 3፡29-30 እንደምንመለከተው ኢየሱስ ከፍ እያለ መሄዱ ለዮሐንስ ሃዘን ሳይሆን ደስታን የሚያመጣለት ነገር ነው፡፡ ተልዕኮው ለኢየሱስ መንገድ ሊጠርግ እንጂ እርሱ ራሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ደጋግሞ የተናገረ በመሆኑ ሰዎች ከኢየሱስ ጋራ ሊያወዳድሩት ሲሞክሩ እንኳን እርሱ ግን ቦታው የት እንደሆነ የገባው አገልጋይ ነበረ፡፡
3. አስቀድሞ ኢየሱስን የተከተለው እንድርያስ ሲሆን፤ ያደረገውም የመጀመሪያ ነገር ወንድሙ ለሆነው ለጴጥሮስ በመንገር ወደ ኢየሱስ ማምጣት ነበረ፡፡
4. የእንድርያስ ወንድም ሶስት መጠሪያ ስሞች እንዳሉት እናያለን፤ እነዚህም ስምዖን፣ ኬፋና ጴጥሮስ ናቸው፡፡ ፊሊጶስ፣ እንድርያስና ጴጥሮስ ሁላቸውም ከቤተ ሳይዳ ከተማ ነበሩ፡፡
5. ኢየሱስ ህግና ነብያት ስለ እርሱ የጻፉለት እንደሆነ፣ ኢየሱስ የዮሴፍ ልጅ መሆኑንና፣ እርሱም መገኛው ከናዝሬት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ለናትናኤል ጥያቄ የሆነው ነገር የኢየሱስ ከናዝሬት ከተማ የመገኘት ጉዳይ ነበረ፡፡ በእርሱ አነጋገር መሰረት የኢየሱስ መምጣት የተመለከተው እንደ በጎ ነገር መሆኑን እንረዳለን፡፡
6. ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነና ደግሞም እርሱ የእስራኤል ንጉስ እንደሆነ አስረግጦ አምኗል፡፡ ወደዚህ ዓይነት የማያወላውል ውሳኔ ላይ ያደረሰውም ነገር ኢየሱስ በቦታው ሳይገኝ ነገር ግን ናትናኤል የነበረበትን ትክክለኛውን ቦታና ሁኔታ ማወቅ መቻሉ ሳይሆን እንደማይቀር ከክፍሉ መረዳት ይቻላል፡፡
7. ለእኔ ጎልቶ የሚታየኝ ልዩነት፣ ፊሊጶስ ለናትናኤል የነገረው አቅዶና ለማግኘት ጥረት አድርጎ ሳይሆን እግዚአብሄር በመንገዱ ላይ ያመጣለትን አጋጣሚ በመጠቀም ሲሆን፤ እንድርያስን ግን ስንመለከት አቅዶና አስቦ ለወንድሜ መንገር አለብኝ ብሎ በእቅድ ያደረገው ነገር መሆኑን እመለከታለሁ፡፡ ለእኔ የምማረው ምስክርነት በእቅድ የሚደረግና በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሄር የሚያመቻቻቸውን ሁኔታዎች በመጠቀም መመስከር እንደሚቻል እማራለሁ፡፡

# ጥናት አራት ዮሐንስ 2፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ፣ የኢየሱስ እናት፣ ደቀ መዛሙርቱ፣ አገልጋዮች፣ የድግሱ ሃላፊ፣ ሙሽራው፣ እንግዶቹ ነበሩ፡፡ ሰርጉ የተካሄደው ከናትናኤል ጋራ ጥያቄና መልስ ባካሄደ በሶስተኛው ቀን ላይ ነበረ፡፡
2. መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጎ ባይነግረንም እንኳን፤ በመላኩ በኩል ይህ ኢየሱስ እንደ ማናቸውም ዓይነት ሰው እንዳልሆነና የተለየ የእግዚአብሄር አገልጋይ መሆኑን ከሙሉ ልቧ ስለተቀበለችው ተአምራትን እስከዚያ ጊዜ ባታይም እንኳን ተአምር ማድረግ የሚችል የልዑል እግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ስለተቀበለች እንደሆነ እገምታሁ፡፡
3. የሚወዳትን እናቱን ለሚወደው ደቀመዝሙር አደራ ለመስጠት የተጠቀመበትን አነጋገር እና ከሁሉም በፊት ከሙታን የተነሳውን ማንነቱን ገልጦ የመጀመሪያ የትንሳኤው ምስክር ላደረጋት መግደላዊት ማርያም የተጠቀመበትን አባባል የንቀት ወይም የስድብ አነጋገር ነው ብሎ ማሰብ በፍጹም ለአዕምሮ የማይመች ነገር ሆኖ ነው የማየው፡፡
4. ማርያም ምንም የተናቀች ወይም እንዳልተከበረች የተሰማት ነገር እንዳለ አናይም፡፡ ማርያም ለኢየሱስ ጥያቄን ካቀረበች በኋላ ከአፏ ያወጣችው ነገር ‹‹የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ›› የሚል ብቻ ነው፡፡ ለማርያም አክብሮት አለኝ ስንል የተናገረችውን ልንሰማት ማለትም ኢየሱስ የሚለንን ሁሉ እንድናደርግ ስለሆነ የምትነግረን ያንን መከተል ይጠበቅብናል ማለት ነው፡፡
5. ለአገልጋዮቹ የኢየሱስ የመጀመሪያው ትዕዛዝ ጋኖቹን ውሃ እንዲሞሉባቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ማርያም የነገረቻቸውን በደንብ ሰምተዋታል የሚያሰኘን፤ ኢየሱስ የሚላቸውን በመታዘዝ ጋኖቹን እስከ አፋቸው ሲሞሏቸው እንመለከታለን፡፡
6. ሁለተኛው ትዕዛዙ ከላዩ ቀድተው ለድግሱ ሃላፊ እንዲሰጡ ነበረ፡፡ እነርሱም በታዘዙት መሰረት ለማርያም ሳይሆን፣ ለህዝቡ ሳይሆን፣ ወይም ለሰርገኞቹ ሳይሆን ኢየሱስ እንደነገራቸው ለድግሱ ሃላፊ ነው የሰጡት፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መማር የምንችለው፤ ኢየሱስን መታዘዝ ብቻ ሳይሆን ካዘዘን ነገር አንዳች ሳንጨምር ወይም ሳንቀንስ ልንታዘዘው እንደሚገባ እናያለን፡፡ 1ኛ ሳሙ 15፡13-19 ይነበብ፡፡
7. የመጀመሪያ ተአምር ያደረገው በሰርግ ቦታ ተገኝቶ ነበረ፡፡
8. ሁለቱ የተጠቀመባቸው ቃላት ‹‹ጥሩ የወይን ጠጅ›› እና ‹‹መናኛ የወይን ጠጅ›› የሚሉት ናቸው፡፡ ሁሉም እያንዳንዱ ለራሱ በልቡ ይመልስ፤ ከክፍሉ የተማሩትና ለወገኖች ሊያካፍት የሚፈልጉት ነገር ካለ ጊዜ ይሰጣቸው፡፡

# ጥናት አምስት ዮሐንስ 2፡12-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ በቤተመቅደስ ውስጥ ያጋጠመው፤ ከብቶችን፣ በጎችን፣ ርግቦችን የሚሸጡና የገንዘብ ምንዛሪ የሚያካሂዱ ሰዎች ናቸው፡፡ ከብቶቹንና በጎችን ሁሉ በጅራፍ ከቤተ መቅደስ እንዳስወጣ እንመለከታለን፡፡
2. እነዚህ አነጋገሮች ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ አድራጎታቸው እጅግ እንደተቆጣ መረዳት እንችላለን፡፡ ይህንን አይነት ወሳኝ እርምጃ የወሰደበት ምክንያት ቁ16 እንደሚነግረን የአባቱ ቤት የንግድ ቤት ሆኖ ስላገኘው ነው፡፡
3. ይህ ያዩት ሁኔታ ለደቀ መዛሙርቱ እንደጠቀማቸው አልጠራጠርም፤ ምክንያቱም በቁ17 ስንመለከት በቃሉ ውስጥ የተጻፈውን እውነት በተግባር ሲፈጸም መመልከት መቻላቸውና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ወደ ቃሉን ወደልባቸው ማምጣቱ ትልቅ መረዳት ነው፡፡ አይሁድ ትምህርት አልቀሰሙም፤ ምክንያቱም በቁ18 ስናይ እንደገና ተአምር ለማየት ነው የሚጠይቁት፡፡
4. ለመገንባት አርባ ስድስት አመት የፈጀ ህንጻ አንተ በሶስት ቀን ውስጥ መልሰህ መገንባት እንዴት ትችላለህ? የሚል ነው፡፡ አይሁድ ሊረዱት የተቸገሩበት ዋናው ምክንያት እርሱ የሚያወራው መንፈሳዊ ነገር ሲሆን፤ እነርሱ ግን የሚያስቡት በሥጋዊ አነጋገር ስለሆነ ነው፡፡
5. ደቀ መዛሙርቱ በተለየ መንገድ አልተረዱትም እላለሁ፤ ምክንያቱም ቁ22 እንደሚናገረው እነርሱም የተናገረው ነገር የገባቸው ከሙታን ከተነሳ በኋላ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ያመኑት፡ አንደኛው መጻህፍትን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኢየሱስ ያለውን ቃል ነው፡፡
6. ስማቸውን ሳይጠቅስ ‹‹ብዙ ሰዎች›› በማለት ይናገራል፡፡ እነዚህ ሰዎች ያመኑት ኢየሱስ ያደረገውን ተአምራት ስላዩ እንደሆነ ከክፍሉ እንረዳለን፡፡ ኢየሱስ በልባቸው ውስጥ ያለውን ስለሚያውቅና ሊሸነግሉት ስለማይችሉ አይታመንባቸውም ነበረ በማለት ጸሐፊው ይነግረናል፡፡
7. በቁ22 ላይ የምናያቸው ያመኑት የእግዚአብሄርን ቃልና ኢየሱስ የተናገረውን ነገር ሲሆን፤ በቁ23 ላይ የምናያቸው ደግሞ እምነታቸውን የመሰረቱት በተመለከቱት ተአምራት ላይ ነበረ፡፡ እምነት ከመስማት፤ መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው፤ ስለሚል ሁለተኛዎቹ ጋራ በትክክል አብሮ ይሄዳል ብዩ አምናለሁ፡፡

# ጥናት ስድስት ዮሐንስ 3፡1-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሰውየው የመጣው በሉሊት ላይ ነበረ፡፡ ይህ ሰው ሰሙ ኒቆዲሞስ ይባላል፣ ከፈሪሳውያን ወገን ነው፣ ከአይሁድ አለቆች አንዱ ነበረ፡፡ ኢየሱስ ከእግዚአብሄር ዘንድ የመጣ መምህር እንደሆነ ያምን ነበረ፡፡
2. በነዚህ ቁጥሮች ላይ የተጀመረው አዲሱ የውይይት አጀንዳ፡ ዳግም የመወለድ ምስጢር ነው፡፡ ኢየሱስ የሚያወራው መንፈሳዊ መወለድን ሲሆን፤ ኒቆዲሞስ ደግሞ በሥጋ የመወለድን ነገር ነው እያወራ ያለው፡፡
3. ኒቆዲሎስ ኢየሱስም በኋላ እንደሚናገረው ትልቅ መንፈሳዊ አስተማሪ ሆኖ ሳለ ይህንን መረዳት መቸገሩ ነው፡፡ የእግዚአብሄርን ነገር መረዳትና መቀበል የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንጂ በምድራዊ እውቀት ወይም ትምህርት ለመረዳት በምንም መንገድ አይቻልም፤ ምክንያቱም ለሥጋዊ ሰው መንፈሳዊ ነገር ሞኝነት ነውና፡፡ 1ኛ ቆሮ 2፡14ትን ተመልከት፡፡
4. ኢየሱስ የኒቆዲሞስን ጥያቄ የመለሰው በጥያቄ ነበረ፡፡ ይህ ዳግመኛ የመወለድ ሃሳብ ኒቆዲሞስን የሚመለከት ብቻ ሳይሆን የሰውን ልጅ በሙሉ የሚመለከት ነገር እንደሆነ እንረዳለን፡፡
5. በእባብ የተነደፉት ሰዎች ሙሴ በምድረበዳ የሰቀለውን የነሃስ እባብ በመመልከት ከሞት መዳን እንደቻሉ ሁሉ፤ በሃጥያት የተነደፉ ሰዎች ሁሉ ደግሞ ከሞት መዳንና የዘለዓለም ህይወትን ማግኘት ከፈለጉ እግዚአብሄር በመስቀል ላይ የሰጠውን ኢየሱስን በማመን ከሞት መዳን እንደሚችሉ ነው፡፡
6. እግዚአብሄር የፍቅሩን መጠን ማረጋገጥ የቻለው አንድያ ልጁን በመስጠት ነው፡፡ ይህ ቁጥር ስለ ተልዕኮው የሚነግረን የመጣው አለምን ለማዳን እንደሆነ ሲሆን፤ በዓለም መፍረድ ደግሞ የኢየሱስ ተልዕኮ እንዳለሆነ በግልጥ ሰፍሮልናል፡፡
7. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ተደጋግሞ የምናየው ቃል ‹‹ብርሃን›› የሚለውን ሲሆን፤ ቃሉም አምስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ብርሃንና የእግዚአብሄር ፍርድ የሚገናኘው፤ እግዚአብሄር ብርሃንን ወደ ዓለም እንደላከ ነገር ግን ሰዎች ከብርሃን ይልቅ ጨለማን መውደዳቸው ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሄር ፍርድ እስከ አሁን ድረስ በላያቸው ላይ እንዳለ እንመለከታለን፡፡
8. ከእግዚአብሄር ፍርድ የሚያመልጡት ሰዎች እግዚአብሄር ወደ ዓለም በላከው ብርሃን ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያመኑ እንደሆኑ በግልጥ ይታያል፡፡ የተቀሩትን እያንዳንዱ ለራሱ መልስ ይስጥበት፡፡

# ጥናት ሰባት ዮሐንስ 3፡22-36 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ሆነ ዮሐንስ ሁለቱም ሰዎችን ሲያጠምቁ ነው የሚታዩት፡፡ ይህ ሁኔታ የተፈጸመው ዮሐንስ ከመታሰሩ በፊት እንደነበረ እንመለከታለን፡፡
2. ለውይይቱ መንስዔ የሆነው ነገር፤ በዮሐንስ ደቀመዛሙርትና በአይሁዶች መሃል የተነሳው ክርክር ነበረ፡፡ ኢየሱስን የገለጡት፤ በዮርዳኖስ ማዶ ካንተ ጋራ የነበረውና ስለ እርሱም አንተ የመሰከርክለት ሰው ብለው ነው የገለጹት፡፡ እነዚህ ሰዎች ለዮሐንስ ችግር አድርገው ያዩት፤ ሰዎች ሁሉ ወደ ኢየሱስ እየሄደ ስለሆነ ወደ ዮሐንስ የሚመጡት ሰዎች ቁጥር የመቀነሱ ሁኔታ ነው ችግር ሆኖ የታያቸው፡፡
3. ‹‹ከላይ ካልተሰጠው በስተቀር ማንም አንዳች ሊቀበል አይችልም›› የሚል መልስ ነው የሰጣቸው፡፡ ለህዝቡ አስቀድሞ ተናግሯቸው የነበረው ነገር በቁ28 ላይ እንደሚታየው፤ እርሱ ክርስቶስ እንዳልሆነና ነገር ግን ከእርሱ በፊት የተላከ መልዕክተኛ እንደሆነ በግልጽ ነግሯቸዋል፡፡
4. ሊሆን የምመኘው ነገር ነው እየተፈጸመ ያለው ማለትም፤ ‹‹እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ይገባል፡፡››
5. በዚህ ዓውደ ምንባብ መሰረት ‹‹ሙሽራይቱ›› በመባል የተጠራቸው አምነው ንስሃ በመግባት የተጠመቁት አማኞች ሲሆኑ፤ ‹‹ሙሽራው›› በመባል የተጠራው ደግሞ ኢየሱስ ነው፡፡ ከዚህ አነጋገር የምረዳው ምንም እንኳን አብዛኛዎቹን ዮሐንስ እያጠመቀ ቢሆንም፤ እነዚህ አምነው እየተጠመቁ ያሉት ሰዎች ሁሉ ንብረትነታቸው የኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ የዮሐንስ እንዳልሆኑ ሲያስገነዝብ ነው፡፡
6. ከላይ የመጣ የሚለውን ከሁሉም ጋራ አወዳድሮ ከሁሉም እንደሚበልጥ ያረጋግጣል፡፡ ከሰማይ የመጣው የሚበልጥበት ምክንያት፡ ከምድር የሆነው የሚናገረው የምድሩን ነገር ሲሆን ከሰማይ የመጣው ግን የሚናገረው የሚናገረው በሰማይ ያየውንና ከሰማይ የሰማውን ነገር ስለሆነ ነው፡፡
7. ህይወትን የማያይ ሰው የተባው በወልድ የማያምነው ሰው ሲሆን፤ የዘላለም ህይወት አለው የተባለው ሰው ደግሞ በወልድ የሚያምን ሰው ነው፡፡ በተጨማሪ ለተጠየቀው ጥያቄ እያንዳንዱ የራሱን መልስ ይስጥበት፡፡
8. እነዚህ ሰዎች የጠበቁት መልስ እንደሚመስለኝ፤ በቅንዓት ተሞልቶ ሄደው እንዲያስቆሙት የሚያዝ፤ ወይም ሌላ የቅራኔ ሃሳብ የሞላበት ነገር እንደሚናገር ሳይጠብቁ እንደማይቀር እገምታለሁ፡፡ ከዚህ መማር የምንችለው ሰዎች ከሙሽራው ኢየሱስ ጋራ እስከተገኘኑና እስከተጣበቁ ድረስ በማን በኩል የሚለው ነገር ጥያቄ ሳይሆን ሁላችንም በደስታ ልንሞላ እንደሚገባን ያስተምረናል፡፡

# ጥናት ስምንት ዮሐንስ 4፡1-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ፈሪሳውያኑ የደረሳቸው ዜና ኢየሱስ ከዮሐንስ በላይ ደቀመዛሙርትን እያፈራ እንደሆነና ብዙዎችንም እያጠመቀ እንደሆነ ነው፡፡ ዜናው እውነትነት ይኑረው እንጂ ሙሉ ለሙሉ ትክክል አልነበረም፤ ምክንያቱም ያጠምቁ የነበሩት ደቀመዛሙርቱ እንጂ ኢየሱስ ራሱ አልነበረም፡፡
2. ወደ ገሊላ ለመድረስ በሰማርያ ማለፍ የግድ እንደነበረ እንረዳለን፡፡ ውይይቱ የተካሄደበት ከተማ ስም ሲካር ይባላል፡፡ ይህች ከተማ ያዕቆብ ለዮሴፍ በሰጠው ቦታ አጠገብ ነበረች፤ በዚህች ከተማም የያዕቆብ የውሃ ጉድጓድ ነበረ፡፡
3. ውይይቱን የከፈተው ኢየሱስ ሲሆን፤ የተጀመረውም እባክሽ የምጠጣው ውሃ ስጪኝ በሚል ነበረ፡፡ ከመልሷ መረዳት የምንችለው ኢየሱስ እንደሚያነጋግራት የጠበቀችው ነገር እንዳልነበረና አይሁዳውያንና ለሳምራዊያን ደግሞ ያላቸውን የጠበቀ ቅራኔ ግልጽ ያደርግልናል፡፡
4. ቁጥሮቹ ያተኮሩበት ቃል ‹‹ውሃ›› የሚለው ሲሆን፤ ይህም ቃል ወደ አስራ አንድ ጊዜያት ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ይህች ሴት በጊዜው ልቧን የያዘውና ልትፈልግ የመጣችው አንድ ነገር ቢኖር ውሃ ስለነበረ፤ ኢየሱስም ደግሞ ለሰዎች የሚሰጠው ትልቅ ነገር ከዚያው ጋራ የተያያዘ የህይወት ውሃ ስለነበረ ነው፡፡
5. ይህች ሴት ያላወቀችው የእግዚአብሄርን ስጦታ ሲሆን ያልተረዳችው ደግሞ ውሃ አጠጪኝ የሚላትን ሰው ማንነት ነበረ፡፡ ሴትየዋ የህይወት ውሃ ይገኛል ብላ የምታስበው አጠገቧ ካለው ጉድጓድ ነው፤ ምክንያቱም ስትመልስለት በቁ11 ላይ ‹‹ጌታዬ መቅጃ የለህም፤ ጉድጓዱም ጥልቅ ነው›› እያለች ከምትናገረው አነጋገር መረዳት ይቻላል፡፡
6. ከዚህ ውሃ የሚጠጣ እንደገና ይጠማል፤ ኢየሱስ ከሚሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ከቶ አይጠማም፡፡ ኢየሱስ የሚሰጠው ውሃ በውስጥ የሚፈልቅ የዘላለም ህይወት ውሃ ምንጭ ይሆናል፡፡ ሴትየዋ ኢየሱስ የሚሰጠውን ውሃ የፈለገችው ከጊዜያዊ ጥማቷ ለመገላገልና ለመቅዳት መመላለስ ስላሰለቻት ነው፡፡
7. ይህ ክፍል ትኩረቱ ‹‹ስግደት›› በሚለው ቃል ላይ ሲሆን፤ ይህም ቃል በተለያዩ መንገዶች አስር ጊዜያት ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ ለሴትየዋ አምልኮ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ማለትም በቦታ የተወሰነ ሲሆን፤ ለኢየሱስ ግን የቦታ ጉዳይ እንዳልሆነ ይታያል፡፡ እሷ የት የሚለው ላይ ስታተኩር፤ ኢየሱስ ግን እንዴት በሚለው ላይ ያተኩራል፡፡
8. ክርስቶስ የተባለ መሲህ እንደሚመጣ ነው እውቀቷ፤ እርሱ ግን እንድታውቅ የፈለገው እርሱ ራሱ መሲሁ ክርስቶስ እንደሆነ እንድታውቅ ነው የፈለገው፡፡

# ጥናት ዘጠኝ ዮሐንስ 4:27-42 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ደቀመዛሙርቱን ያስደነቀው ነገር የኢየሱስ ከሴት ጋራ ሲነጋገር ማግኘታቸው ነበረ፡፡ እኔን የጴጥሮስ ዝምታ ያስደንቀኛል፤ ምክንያቱም እርሱ ለማናቸውም ነገር ለመጠየቅም ሆነ መልስ ለመስጠት ወደኋላ ስለማይል ነው፡፡
2. ሴትየዋ ያደረገቸው ነገር ወደ ከተማ መመለስና ለህዝቡ ስለኢየሱስ መናገር ነበረ፡፡ ፊሊጶስና እንድርያስ ከመሰከሩት ምስክርነት የሚለይበት መንገድ እነሱ መሲሁን ክርስቶስን ማግኘታቸውን በእርግጠኛነት ሲናገሩ፤ ይህች ሴት ግን እርግጠኛነትን በማያሳይ መንገድ ‹‹ክርስቶስ ይሆን እንዴ›› ነው ያለቸው፡፡ እንስራውን ትታ መሄዷ የሚያሳየኝ ልትቀዳ ከመጣችው ውሃ የበለጠ ነገር እንዳገኘች የገባት ሲሆን፤ ለዚህ ይመስለኛል እንስራዋ ትዝም ያላላት፡፡
3. ውይይታቸው በምግብ ዙሪያ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በሁለቱ መሃል በተካሄደው ውይይት እንዳልተግባቡ አያለሁ፤ ምክንያቱም እርሱ የሚናገረው ስለ ሰማያዊ ምግብ ሲሆን፣ ደቀመዛሙትቱ ደግሞ የሚናገሩት ስለ ምድራዊ ምግብ ነበረ፡፡
4. አንደኛው የላከውን ፈቃድ ማድረግ ሲሆን ከዚያ ጋራ አብሮ የማይነጣጠል ሁለተኛው የላከውን ሥራ መፈጸም ናቸው፡፡ ምግብ ካልበላነው የሚርበን፣ ከበላነው ደግሞ የሚያጠግበን ወይም የምንረካበት ነገር ሲሆን ኢየሱስንም የሚያረካውና የሚያጠግበው የላከውን ፈቃድ ሲያደር በመሆኑ ለዚህ ነው ለእርሱ ምግቡ ሆኖ የተጠቀሰው፡፡
5. በቁ39 ላይ ያሉት ያመኑት የእርሷን ምስክርነት በመስማት ሲሆን፤ በቁ41 ላይ ያሉት ደግሞ ቃሉን ሰምተው ነው ያመኑ ናቸው፡፡ ከዚህ መማር የምንችለው፤ በህይወታችን ጌታ ያደረገውን ነገር ለሰዎች ስንናገር ምስክርነታችንን ሰምተው ሊያምኑ እንደሚችሉ ስናይ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉ ተሰብኮላቸው ጌታን የሚቀበሉ እንዳሉ በማየት ጌታ ሁለቱንም መንገዶች ሊጠቀም እንደሚችል እንመለከታለን፡፡
6. የወሰዱት ሁለተኛው እርምጃ ራሳቸው ወደ ኢየሱስ ቀርበው ከእርሱ አፍ ቃሉን መስማት ነበረ፡፡ በራሳቸው ከሰሙት በኋላ የደረሱበት እውነት ኢየሱስ እርሱ የዓለም አዳኝ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ መማር የምንችለው ነገር ምንም እንኳን የሰዎች ምስክርነት ወደ ኢየሱስ ሊያመጣን ቢችልም፤ የእርሱን እውነተኛ ማንነት መረዳት የምንችለው ቃሉን ስናጠናና ከእርሱ ስንሰማ እንደሆነ እንማራለን፡፡
7. ከጥንት ጀምሮ የነበሩትን የመሲሁን መምጣት ያበሰሩትን ነብያት ሁሉ የሚጨምር ሲሆን፤ በተለይም ግን እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ያሉትን የሰዎችን ልብ ለንስሃ ያዘጋጁትን ሁሉ ሊጨምር እንደሚችል አያጠራጥርም፡፡ ደቀመዛሙርቱ ይህንን እውነት መረዳት የነበረባቸው ምክንያት፤ አዝመራው ያለድካም  የተገኘ እንዳልሆነ የሌሎችም ድካም እንዳለበት እንዲገነዘቡ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች ተሰብኮላቸው ወደ እምነት ባይመጡ ሌላ አዝመራ ሰብሳቢ እግዚአብሄር ሊልክ እንደሚችል እንዲያስቡ ይሆናል፡፡

## ጥናት አስር ዮሐንስ 4፡43-54 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ሰዎች የተቀበሉት በደስታ ሲሆን፤ ምክንያቱም በቁ 45 ላይ እንደሰፈረው በኢየሩሳሌም ያደረገውን ተአምራት ሁሉ ስላዩ ነበረ፡፡
2. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናያቸው ሰዎች፡ ኢየሱስ፣ የቤተ መንግሥቱ ሹምና ልጁ ናቸው፡፡ ይህ ሰው የሚኖረው በቅፍርናሆም ነው፣ ልጁ ታሞበታል፣ የቤተመንግሥት ሹም ነው፡፡
3. በወሬ ሰምቶ ነው፡፡ ልጁን እንዲፈውስለት ነው የለመነው፡፡ ኢየሱስ ልጁን ሊፈውስ እንደሚችል ያወቀ የሚመስለኝ፤ ቁ46 ላይ እንደሚናገረው ይህች ከተማ ኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምራቱን ያደረገባት እንደሆነች እናነባለን፤ ስለዚህም ይህ ሰው ኢየሱስ ከዚህ ቀደም ያደረገውን ተአምራት ስለሚያውቅ ያንን ተአምር ያደረገ ይህንንም ማድረግ አይሳነውም በሚል እምነት ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡
4. ይህ ሰው ጥያቄውን ያቀረበው በልመና ነው፡፡ ይህ ሰው ሹም ሆኖ በልመና መቅረቡ የሚነግረኝ እውነትም ከኢየሱስ የሚገኝ ነገር እንዳለ ከልቡ እንዳወቀ እረዳለሁ፡፡ ኢየሱስ የመለሰለት መልስ ‹‹መቼውንም እናንተ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ አታምኑም›› የሚል ነበረ፡፡
5. ሰውየው ኢየሱስ የተናገረውን ሰምቷል፤ ነገር ግን ተስፋ ቆርጦ ልመናውን ሳያቋርጥ እባክህ ድረስልኝ በማት ሲማጠነው እናያለን፡፡ ለሁለተኛው ጥያቄው የኢየሱስ ምላሽ ‹‹ልጅህ በህይወት ይኖራልና ሂድ›› የሚል ነበረ፡፡
6. ይህ ሁኔታ ሊነግረን የሚችለው እውነት ሰውየው ኢየሱስ በተናገረው ቃል ልጁ እንደተፈወሰ እምነቱ ሙሉ ስለነበረ ወደ ቤቱ መሄድና ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ስላላገኘው እግረ መንገዱን ማድረግ ያለበትን ጉዳዮቹን ፈጻጽሞ ለመሄድ የወሰነ ሳይሆን እንደማይቀር እገምታለሁ፤ ምክንያቱም እርግጠኛ ባይሆን እስቲ ቶሎ ሄጄ እውነት እንደሆነ ላረጋግጥ ማለት የነበረበት ይመስለኛል፡፡
7. ሰውየው ያመነው ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ነው፡፡ ይህ ሰው ማመኑን ያረጋገጠበት መንገድ ኢየሱስን መለመን አልቀጠለም፤ ነገር ግን የተነገረው ቃል እውነት እንደሆነ አምኖ ጉዞውን ነው የቀጠለው፤ ደግሞም አገልጋዮቹን ሲያገኝ እርሱ ሳይሆን የልጁን ደህንነት የጠየቀው እነርሱ ናቸው ደህንነቱን የነገሩት፤ እርሱ የጠየቃቸው የተፈወሰበትን ሰዓት ነበረ፡፡

# ጥናት አስራ አንድ ዮሐንስ 5፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በኢየሩሳሌም ውስጥ ትገኛለች፣ በበጎች በር አጠገብ ትገኛለች፣አምስት ባለ መጠለያ መመላለሻዎች ነበሯት፣ ስሟ ቤተሳይዳ ይባላል፡፡ በዚህ ቦታ የተሰበሰቡት፤ አካለ ስንኩላን፣ አይነ ስውሮች፣ አንካሶችና ሽባዎች ነበሩ ይለናል፡፡ ስለቁጥራቸው የምናውቀው ነገር ቢኖር ቁ3 መጀመሪያ ላይ ‹‹በዙ›› በማለት ይናገራል፡፡
2. ሰዎቹ በዚያ ለመገኘታቸው ምክንያት በአንድ ቃል ‹‹ለፈውስ›› እላለሁ፡፡ ውሃው መቼ እንደሚንቀሳቀስ የሚያውቅ ሰው ስለሌለና ማስጠንቀቂያም ስለማይሰጥ በአንድ በኩል መጠበቅ ሲኖር፤ በሌላ በኩል ደግሞ መንቀሳቀሱ እየተጠበቀ ደግሞ ሳይተኛ መክረም ስለማይቻል ከሙሉ ልብ ያልሆነ መኝታ እንደሚተኙ ሲሆን፤ መኝታ የሚለውም በሌላ በኩል ደግሞ ብዙዎቹ ምናልባትም መንቀሳቀስ የማይችሉ ዓይነቶች ስለሚሆኑ እዚያው ተጋድመው መጠበቃቸውን ሲያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡
3. ውሃውን ያናውጥ የነበረው የጌታ መልዓክ ሲሆን፤ ያናውጥ የነበረውም አልፎ አልፎ እንደነበረ በቁ4 ላይ እናነባለን፡፡ በዚህ ስፍራ ለመፈወስ መስፈርት የሆነው ነገር ቀድሞ ወደ መጠመቂያይቱ መግባት፤ ማለትም በእሽቅድድሙ አንደኛ ሆኖ መገኘት ብቻ ነበረ፡፡
4. ዮሐንስ ይህንን ሰው ‹‹ለሰላሳ ስምንት ዓመታት ህመምተኛ ሆኖ የኖረ ሰው›› ብሎ ነው ያስተዋወቀው፡፡ ‹‹ልትድን ትወዳለህን?›› ብሎ ነው ሰውየውን የጠየቀው፡፡ ለብዙዎች ይህ ጥያቄ ስሜት የማይሰጥ ሆኖ የምናይበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ ይህንን ያህል ዘመን የታመመን ሰው ለመዳን ትፈልጋለህ ወይ? ብሎ መጠየቅ ለሰው የማይዋጥ ሲሆን፤ በተጨማሪ ደግሞ ይህ ሰው ከበሽታው ለመዳን በዚህ ቦታ የውሃ መንቀሳቀስ እየጠበቀ ያለው የዚህ ዓይነት ጥያቄ መጠየቁ ሊያስገርም ይችላል፡፡
5. የህመምተኛው መልስ፤ ‹‹ጌታዬ ውሃው በሚናወጥበት ጊዜ ወደ መጥመቂያይቱ የሚያወርደኝ ሰው የለኝም›› የሚል ነበረ፡፡ ኢየሱስ ለጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ አላገኘም፤ ምክንያቱም እርሱ የጠየቀው ለመዳን መፈለግ አለመፈለጉን ሲሆን፣ ሰውየው የዘረዘረው ግን እስከዛሬ ያልተፈወሰባቸውን ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው የሰው ማጣት ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የፍጥነት/ጉልበት ማጣት ናቸው፡፡
6. ለኢየሱስ ይህ እንቅፋት አልሆነበትም፡፡ ለዚህ ህመምተኛ ምንም ሰው ሳያስፈልገው ጉልበቱንም ሁሉ መልሶለት ራሱን መሸከምና ወደ ውሃው ማስገባት ያልቻለውን፤ አልጋውን መሸከም እንዲችል እንዳደረገው እንመለከታለን፡፡
7. ኢየሱስ ለሰውየው የሰጠው ማስጠንቀቂያ ‹‹እነሆ ተፈውሰሃል፤ ከእንግዲህ ግን ሃጥያት አትስራ፤ ያለዚያ ከዚህ የባሰ ይደርስብሃል›› የሚል ነበረ፡፡ እኛም የነፍስ መዳን የተቀበልን ሁላችን፤ አንዴ ድኛለሁ ብለን የሃጥያት ኑሮን ለመኖር ብንቀጥል እግዚአብሄር ከሃጥያት ጋራ ህብረት ስለሌለውና የሚወደውን ሁሉ ስለሚቀጣው መለኮታዊ ቅጣት እንደሚያገኘን የታወቀ ነገር ነው፡፡ ዕብ 12፡4-6

# ጥናት አስራ ሁለት ዮሐንስ 5፡16፡30 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስን ያሳደዱት መልካም በማድረጉ ማለትም ሰውየውን በመፈወሱ ሲሆን፤ የእርሱ ምላሽም አባቱ እስካሁን እየሰራ እንደሆነና፤ እርሱም መልካም ከመስራት እንደማያቆም ነበረ የነገራቸው፡፡
2. በብዛት የምናያቸው ቃላት፤ አብ እና ወልድ የሚሉት ሲሆኑ፤ እያንዳንዳቸው ሰባት ሰባት ጊዜ ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ እንዲያውም ይበልጥ አጠናከረው እላለሁ፤ ምክንያቱም ወረድ ብሎ ባሉት ቁጥሮች ላይ ከአባቱ ጋራ ያለውን ጥልቅ የሆነ ግንኙነት በስፋትና በማያዳግም መንገድ ሲገልጥ ይታያል፡፡
3. አንደኛው ሰንበትን መሻሩ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሄር ጋራ እኩል ማድረጉ ነበረ፡፡
4. ‹‹አንድነት›› እላለሁ፡፡ በነዚህ ሶስት ቁጥሮች ላይ የተተኮረው፤ ህይወት መስጠት፣ ፍርድ መፍረድና ሌላው ደግሞ ክብር ናቸው፡፡ ሙታንን ማስነሳትና ህይወት መስጠት የአብም የወልድም ሃለፊነት ሆኖ ነው የተነገረን፡፡
5. የፍርድን ሃላፊነት የተቀበለው ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ ሰዎች ሁሉ ክብር እንዲሰጡተ የተገባው ለአብ የሚሰጠው ክብር ሁሉ ለወልድም እንዲሰጥ ተነግሯል፡፡ በማንኛውም አይነት ግንኙነት፤ በትዳር ቢሆን እያንዳንዱ የተሰጠውና ሊያከናውን የሚጠበቅበት ሃላፊነት መኖሩ እኩል ያለመሆንን የሚያመለክት ነገር አድርጎ መመልከት ትክክል እንዳልሆነ መማር እንችላለን፡፡
6. የኢየሱስን ቃል መስማትና ኢየሱስን በላከው ማመን ናቸው፡፡ ይህ ሰው ከሞት ወደ ህይወት መሻገሩና፣ ወደፊት ወደፍርድ እንደማይመጣ ያረጋግጥልናል፡፡ የኢየሱስን ስብከት የሰሙ ሁሉ ይድናሉ ማለቱ ሳይሆን፤ መስማት የሚለው መታዘዝን የሚጨምር የማለት ሃሳብ ነው ያለው፡፡
7. ሰዎች ሁሉ ማለትም መቃብር ውስጥ ያሉ ሁሉ ናቸው፡፡ እነዚህን ሰዎች የሚከፍላቸው በሁለት ሲሆን፤ መልካም የሰሩና ክፉ የሰሩ ይላቸዋል፡፡
8. በእነዚህ ሁለት ሰሚዎች መሃል ያለው ዋናው ልዩነት፤ በቁ24 ላይ ያሉት ሰምተው አቤት ለማለትና ታዘው የዘላለም ህይወት ለመውረስ ዕድል ያላቸው ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ ግን ዕድላቸውን የጨረሱና ሌላ ውሳኔ ለማድረግ ዕድል የሌላቸው ሰዎች ናቸው፡፡

# ጥናት አስራ ሶስት ዮሐንስ 5፡31-47 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በብዛት የተጠቀሰው ቃል ‹‹ምስክርነት›› የሚለው ቃል ነው፤ ይህም ቃል በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተለያየ መንገድ አስር ጊዜ እናገኘዋለን፡፡
2. ኢየሱስ ይህንን ሲል ምስክርነቴ ትክክል አይደለም ማለቱ ሳይሆን 2ኛ ቆሮ 10፡17-18 እንደሚናገረው ሌላ ሰው ሲያመሰግን እንጂ ራስን ማመስገን መጽሃፍ ቅዱሳዊ ሃሳብ አይደለም፡፡ ለእኛም ከዚህ የምንማረው ነገር ስለራሳችን መልካም የምንናገርና ራሳችንን የምንከብ ሳንሆን ሰዎችና በተለይም እግዚአብሄር መልካም የሚናገርልን ዓይነት ሰዎች መሆን እንደሚኖርብን እንማራለን፡፡
3. ኢየሱስ ቢያንስ ሶስት ምስክሮችን እንደሚጠራ አያለሁ እነዚህም፡ ዮሐንስ (ቁ33)፣ ሥራው (ቁ36)፣ አብ (ቁ37)፤ ማቴ 18፡16 ምስክርነት በሁለት ወይም በሶስት እንደሚጸና ይነግረናል፡፡
4. ኢየሱስ ይህንን ያህል ከአብ መላኩን ለማረጋገጥ እየሞከረ ያለው እነዚህ ሰሚዎቹ እንዲድኑ ፈልጎ መሆኑን በግልጽ ይነግራቸዋል፡፡ ኢየሱስ ለነዚህ ሰዎች የነገራቸው ሶስቱ ነገሮች፡ አብን ከቶ እንዳልሰሙት፣ መልኩን እንዳላዩትና፣ የእግዚአብሄር ፍቅር በልባቸው ፍጹም እንደሌለ ነው፡፡
5. የመጀመሪያው ኢየሱስ በአባቱ ስም ሲመጣ ሳይቀበሉት፤ ሌላው ግን በራሱ ስም ሲመጣ ይቀበሉታል፣ ሁለተኛው እርስ በእርሳቸው ክብርን ሲቀባበሉ ነገር ግን ከእግዚአብሄር የሚመጣውን ክብር አይፈልጉም፡፡ ይህንን ማድረጋቸው ያስቀረባቸው በረከት ወደ እምነት ለመምጣት ከልክሏቸዋል፡፡
6. ለመዳናቸው የሚመኩበት በኢየሱስ አነጋገር ሙሴን ማመናቸው ሲሆን፤ ሙሴ ከማዳን ይልቅ የሚፈርድባቸው እንደሆነ ነው የሚነግራቸው፡፡
7. ምክንያቱም ሙሴ የጻፈው ሁሉ ስለ ኢየሱስ ስለሆነ ለያይቶ ማየት አይቻልም፡፡ እነዚህ ሰዎች ሙሴ የጻፈውን አምነው ቢሆን ኖሮ በቁ47 መሰረት ኢየሱስ የሚናገረውን ያምኑ ነበር ማለት ነው፡፡
8. እነዚህ ሰዎች የዘላለም ህይወት የሚገኘው መጻህፍትን በመመርመር እንደሆነ የሚያምኑ ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን ትክክለኛው የዘላለም ህይወት የሚገኝበት መንገድ ወደ እርሱ በመምጣት መሆኑን ይነግራቸዋል፡፡

<u>ጥናት አስራ አራት ዮሐንስ 6፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ኢየሱስ፣ ደቀመዛሙርቱ፣ እንጀራና አሳ የያዘው ልጅ፣ ብዙ ህዝብ፡፡ ይህ ሁሉ ህዝብ ወደ ኢየሱስ የመጣው በቁ2 ላይ እንደምናነበው ኢየሱስ ያደረገውን ተአምራቶች ስላዩ እንደሆነ ይነግረናል፡፡
2. ጥያቄው ‹‹እነዚህ ሰዎች እንዲበሉ እንጀራ ከየት እንግዛ;›› የሚል ነበረ፡፡ ይህ ለእኛ መልካም ዜና የሚሆነው፤ ለእነርሱ ለሥጋቸው በሚያስፈልጋቸው የተቆረቆረው ኢየሱስ ለእኛም የእለት እለት ኑሯችን እንደሚያስብልን እንግራለን፡፡
3. ፊሊጶስን የጠየቀበት ምክንያት ሊፈትነው እንደሆነ ቁ6 ይነግረናል፡፡ ፈተናውን ፊሊጶስ አልፏል ብዬ አልልም፤ ምክንያቱም ብዙ ዓይነት ተአምራትን ያደረገው ኢየሱስ በአጠገቡ እያለ እርሱ ሊያደርግ የሚችለው ነገር እንዳልሆነና ከእርሱ በላይ የሆነ ነገር አስመስሎ ሲናገር ስለምንሰማው በቂ እምነት አልነገረውም ማለት እንችላለን፡፡
4. እንድርያስ ኢየሱስ አንድ ነገር ማድረግ እንደሚችል ያወቀ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛነት የጎደለው እንደሆነ እመለከታለሁ፤ ምክንያቱም ይህ ባይሆን ከአምስት ሺህ ላላነሰ ሰው አምስት እንጀራና ሁለት ዓሳ አለ አይልም ነበረ፡፡ በፊሊጶስና በእንድርያስ እምነት የሚታየኝ ልዩነት፣ ፊሊጶስ ፈጽሞ ኢየሱስ ያደረገው ማናቸውም ተአምር ከዚህ ጋራ ማገናዘብ የቻለ አይመስለኝም፤ እንድርያስ ግን የጎደለው ነገር እርግጠኛ ሆኖ ይኸውልህ እንዲበዛ አድርገው ማለት ነው ያቃተው እላለሁ፡፡
5. ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ህዝቡን እንዲያሰናብት ነበረ የመከሩት፤ እርሱ ግን አላሰናብታቸውም እናንተው የሚበሉት ስጧቸው አለ፡፡ ኢየሱስ ይህንን እንዲያደርግ ያስገደደው ወይም የገፋው ነገር ርህራሄው እንደሆነ በማቴዎስ ላይ ያነበብነው ክፍል ያስረዳናል፡፡
6. ወደ አለም የሚመጣው ነብይ ይህ መሆን አለበት ወደሚለው አስተሳሰብ አደረሳቸው፡፡ ከዚህም ተነስተው ሊያነግሱት እንደፈለጉ ይታያል፡፡ በአስተሳሰባቸውና ሊያደርጉ ባሰቡት ነገር መሃል የማየው ቅራኔ ወደ ዓለም የሚመጣው ነብይ እንጂ ንጉስ ስላላሉት እንዴት ሊያነግሱት እንደፈለጉ አላውቅም፡፡
7. የሰው ቁጥር ምናልባት ሴቶቹና ልጆች ተደምረው አምስት ሺህ ቢሆኑ በአጠቃላይ ቁጥሩ ከወንዶቹ ጋራ ወደ አስር ሺህ የጠጋል እላለሁ፡፡ ለደቀመዛሙርቱ ስለአቀማመጥ የሰጠው መመሪያ ህዝቡን በአምሳ በአምሳ እያረጉ እንዲያስቀምጡ ነበረ፡፡ የደቀመዛሙርቱ ድርሻ ህዝቡን በታዘዙት መሰረት ማስቀመጥ፣ ለህዝቡ እንጀራውንና አሳውን ማቅረብ፤ ለራሳቸው መብላትና፣ ተበልቶ የተረፈው ደግሞ አንድም ሳይወድቅ መሰብሰብ ነበረ፡፡
8. አንደኛው ህዝቡን ማሰናበት፤ ማትም ችግሩን መፍታት ሳይሆን ችግሩን መግፋት፤ ሁለተኛው ፊሊጶስ ችግሩን በገንዘብ ለመፍታት የሞከረው፤ ሶስተኛው እንድርያስ ችግሩ እንዴት መፍትሄ እንደሚያገኝ ባያውቅም ሃሳብ ሰንዝሯል፤ በአራተና ደረጃ ጌታ የሰጠው ትክክለኛ መፍትሄ ነው፡፡

## ጥናት አስራ አምስት ዮሐንስ 6፡16-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ደቀመዛሙርቱ ለብቻቸው የሆኑት ኢየሱስ በቁ15 ላይ ከፍ ከፍ ሊያደርጉት ማለትም ሊያነግሱት ሲያስቡ ብቻውን ወደ ተራራ ገለል እንዳለና ከዚያም በቶሎ እንዳልተመለሰ እንረዳለን፡፡ ደቀመዛሙርቱ ለመሻገር ሲነሱ ጊዜው መሽቶ ነበረ፣ ኢየሱስ ወደ እነሱ ገና አልተመለሰም ነበረ፣ ሃይለኛ ነፋስ ይነፍስ ስለነበረ ባህሩ ይናወጥ ነበረ፡፡
2. ተደርጎና አይተውት የማያውቁት ነገር ማለትም ኢየሱስ በውሃው ላይ እየተራመደ መሄዱ ነበረ ያስደነገጣቸው፡፡ ይህንን ሲያዩ በቀጥታ የገሙቱት ነገር ምትሃት እንጂ ሰው ነው ብለው አላሰቡም፡፡
3. በቁ22-24 ላይ የተጻፈውን ሃሳብ በራሳቸው አማርኛ የተወሰኑ ሰዎች እንዲናገሩ እድል ይሰጥ፡፡ ኢየሱስን ሲያገኙት የጠየቁት ጥያቄ ››ረቢ መቼ ወደዚህ መጣህ?›› የሚል ነበረ፡፡
4. ሰዎቹ የተከተሉት እንጀራ ስለበሉና ስለጠገቡ፤ ማለትም ለሥጋቸው የሚሆነውን ፈልገው ነው፡፡ ኢየሱስ የሚመክታቸው በቅድሚያ በነፍሳቸው ላይ እንዲያተኩሩ ነው፡፡
5. ሰዎቹ የጠየቁት ጥያቄ ‹‹የእግዚአብሄርን ሥራ ለመስራት ምን ማድረግ አለብን?›› የሚል ሲሆን፤ ኢየሱስ የሰጣቸው መልስ ደግሞ ‹‹እርሱ በላከው ታምኑ ዘንድ ይህ የእግዚአብሄር ሥራ ነው›› የሚል ነበረ፡፡
6. ማህተም የነገሮችን እውነተኛነት ለማረጋገጥ፣ የዶኩመንቶችን ህጋዊነት ለማረጋገጥና ለመሳሰሉት ሁኔታዎች የምንጠቀምበት ሲሆን እግዚአብሄርም የኢየሱስን ተልዕኮ ትክክለኛነት በተአምራቶችና ድንቆች፣ ከሞትም በማስነሳት ጭምር አረጋግጦለታል፡፡
7. በቁ26-27 ለምድራዊ እንጀራ ኢየሱስን መከተል ቅድሚያ መስጠታቸውን ኢየሱስ ለሰማያዊው እንጀራ ቅድሚያ እንዲሰጡ እንደነገራቸው፤ በ28-29ኝም ላይ እርሱ በላከው ማመን የመጀመሪያን ሥፍራ ሊይዝ ሲገባው፤ የእግዚአብሄርን ሥራ መስራትትን ቅድሚያ መስጠታቸው ነገርን እንደሚያገላብጡ ያሳየናል፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት ዮሐንስ 6፡30-51 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህ አነጋገር ቶማስን ያስታውሰኛል፡፡ እነዚህ ሰዎች ተአምር ቢያዩም ኢየሱስን ለማመን ልባቸው የተዘጋጀ መስሎ አይታየኝም፤ ምክንያቱም ቁ26 ላይ እንደምናነበው ሰዎቹ ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዎችን በአምስት እንጀራ የመገበበትን ተአምር አይተው ያላመኑ ስለሆኑ ነው፡፡
2. ‹‹እንጀራ›› የሚለው ቃል ሲሆን በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስድስት ጊዜ እናገኘዋለን፡፡ ይህ ቃል በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው በአብዛኛው ወደ ኢየሱስ የሚጠቁም ነው፡፡
3. እንጀራው የእግዚአብሄር እንጀራ ነው፣ ከሰማይ የሚወርድ ነው፣ ህይወትን የሚሰጥ ነው፡፡ በቁ34 ላይ ሰዎቹ ይህንን ጥያቄ ሲያቀርቡ የተናገረውን እንዳልተረዱት ነው የሚገባኝ፤ ምክንያቱም እነርሱ ሁልጊዜ ስጠን ሲሉ በየለቱ መብላትን ማለትም ምድራዊውን እንጀራ እንደጠየቁ ነው የሚመስለው ይህንንም በቁ41 ላይ በማጉረምረማቸው ሲገለጥ እንመለከታለን፡፡
4. ሰማያዊውን እንጀራ መብላት ማለት ወደ ኢየሱስ መምጣት ወይም በኢየሱስ ማመን ማለት ነው፡፡ ቁ37 ‹‹ወደእኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጪ አላወጣውም፡፡›› ቁ39 ‹‹የላከኝ ፈቃድ ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ ሳይጠፋብኝ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሳ ነው፡፡›› ቁ40 ‹‹የአባቴ ፈቃድ ወልድን አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው ነው፡፡›› የሚሉት ናቸው፡፡
5. ለእነዚህ አይሁዶች ሊዋጥላቸው የተቸገሩበት ሃሳብ ‹‹ከሰማይ ወረድሁ›› የሚለው አነጋገር ሲሆን፤ ለዚህም ምክንያት የሆነው በሰፈራቸው ያደገ፣ አባቱንና እናቱን የሚያውቋቸው በመሆኑ ነው፡፡
6. ከዚህ አነጋገሩ የምንማረው እውነት፣ ሰው ደህንነትን ለማግኘት ወይም ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን እግዚአብሄር ራሱ ሊስበውና ሊጠራው እንደሚያስፈልግ እንማራለን፡፡
7. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በብዛት የተጠቀሰው አንድ ቃል ‹‹እንጀራ›› የሚለው ቃል ሲሆን፤ በዘሬው ምንባብም ውስጥ በሰፊው ቦታ የተሰጠውና ኢየሱስ በተደጋጋሚ የተናገረው ቃል ‹‹እንጀራ›› የሚለው ነው፡፡ በቁ42 አይሁድ የተሰናከሉበትና ኢየሱስ መልሶ መጠቀም ያላቆመው ‹‹ከሰማይ ወረድኩ›› የሚለው ሃሳብ ነው፡፡ በእኔ አስተሳሰብ ቃሉን መጠቀም ያላቆመበት ምክንያት እርሱ እውነትም ከሰማይ የወረደ እውነተኛ እንጀራ በመሆኑና ይህም እውነት ሁሉም ሊቀበሉት ስለሚያስፈልግ ነው፡፡
8. ሰዎቹ መናን የሰጣቸው ሙሴ እንደሆነ ነው የሚናገሩትና የሚያስቡት፣ ኢየሱስ ግን ይህ አስተሳሰብ የተሳሳተ መሆኑንና ከሰማይ እንጀራን የሰጣቸው እግዚአብሄር እንደሆነ ነው የሚያስገነዝባቸው፡፡

# ጥናት አስራ ሰባት ዮሐንስ 6፡52-71 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ቁ52 ላይ እንደምናነበው ያከራከራቸው የነበረው ነገር ‹‹እንበላ ዘንድ ይህ ሰው ሥጋውን እንዴት ሊሰጠን ይችላል?›› የሚለው ሃሳብ ነበረ፡፡ የክርክራቸው መሰረት መንፈሳዊውን እውነት ያለመረዳት ነው፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ሥጋውን እንዲበሉ ሲል ቀጥተኛ ትርጉሙን ወስደው ነው የረከረከሩት፡፡ ትርጉሙ ወደ ኢየሱስ መምጣትና በኢየሱስ ማመን መሆኑ ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡
2. አንደኛው አባቶች የበሉት ሥጋዊ እንጀራ ሲሆን ኢየሱስ የሚሰጠው መንፈሳዊ እንጀራ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ መናውን የበሉት አባቶች ሁሉ ሞተዋል፤ ኢየሱስ የሚሰጠውን እንጀራ የሚበላ ሁሉ ግን አይሞትም፡፡ ይህንን ያስተማረውም በቅፍርናሆም ከተማ በምኩራብ ውስጥ ነበረ፡፡
3. ትምህርቱ የከበደው ለብዙዎች ሰሚዎቹ እንደነበረ ቁ60 ይነግረናል፡፡ ለህዝቡ የከበዳቸው ትምህርት የእርሱን ሥጋ መብላት እንዳለባቸው የተናገረው እንደሚሆን በተለያዩ ክፍሎች የምናነበው ይነግረናል፡፡
4. የሰዎቹን ማጉረምረም ያወቀው ቁ61 እንደምናየው ‹‹በራሱ ተረድቶ›› ስለሚል ማንም የነገረው ሰው የለም፡፡ ለሚያጉረመርሙት ሰዎች በዚህ ክፍል የተናገረው በዚህ ዓይነቱ ነገር ካጉረመረማችሁ ሌላ የበለጠ ነገር ብታዩማ ምን ልትሆኑ ነው የሚል ነበረ፡፡
5. ሰዎቹ ያጉረመረሙት አነጋገሩን በሥጋዊ አመለካከት እንጂ መንፈሳዊ ትርጉም እንዳለው ስላልተረዱ በመሆኑ እርሱ የነገራቸው ቃል በመንፈሳዊ ዓይን መታየት ያለበት መሆኑንና በዚያም ዓይን ለተመለከተው ሰው ህይወት እንደሚሆንለት ለማስተማር እንደሆነ ነው የሚገባኝ፡፡
6. በቁ64 መሰረት አለማመናቸውን የተረዳው ቀድሞ ወይም ይህ ከመሆኑ በፊት እንደነበረ ይታያል፡፡ ከነዚህ ቁጥሮች የምንማረው ማንኛውም ሰው ወደ ክርስቶስ ለመምጣት አብ ሊስበው ወይም ከአብ ሊሰጠው እንደሚያስፈልግ እንማራለን፡፡
7. እነዚህ ሰዎች መጨረሻቸው ወደኋላ መመለስና ከዚያን ጊዜ በኋላ እንዳልተከተሉት ግልጽ አድርጎ ይነግረናል፡፡ እንደ ኢየሱስ አነጋገር ከሆነ እነዚህ ሰዎች ቀድሞውንም ያመኑ ሰዎች እንዳልነበሩ በድፍረት መናገር እንችላለን፡፡ ይህንን ማለት የማንችልበት ምክንያት እንደ ኢየሱስ የሰዎችን ልብ ማወቅ ስላልተሰጠን አፋችንን ሞልተን በድፍረት መናገር አንችልም፡፡
8. ያለ ኢየሱስ መኖር እንደማይቻል የተረዳው ጴጥሮስ ሲሆን፤ የተናገረውም ስለራሱ ብቻ ሳይሆን አስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት በመወከል ነበረ፡፡ ያለ ኢየሱስ መኖር አይቻልም ያለው፤ የዘላለም ህይወት ቃል ያለው በኢየሱስ ዘንድ ነው፣ ኢየሱስ ደግሞ የእግዚአብሄር ቅዱስ ወይም እግዚአብሄር የለየው ነው፡፡
9. መልስ የሰጠው ‹‹እናንተም ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ?›› ለሚለው የኢየሱስ ጥያቄ ነበረ፡፡ ይህ የኢየሱስ ድርጊት የሚያስተምረን፤ ለሰዎች ስሜትና ከቤተ ክርስትያን ይቀራሉ ብለን የእግዚአብሄርን እውነት መቀየጥ እንደማይኖርብን ጥርት ባለ መንገድ ያስተምረናል፡፡

# ጥናት አስራ ስምንት ዮሐንስ 7፡1-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ የሚያስተምርበትን ቦታ መቀየር ያስፈለገው ምክንያት በይሁዳ ሊገድሉት ስለፈለጉ ነበረ፡፡ ወንድሞቹ ደግሞ ይገፋፉት የነበረው ተመልሶ ወደ ይሁዳ እንዲሄድ ነበረ፡፡
2. ወንድሞቹ የሰጧቸው ምክንያቶች፤ ተከታዮችህ ወይም ደቀመዛሙርትህ ተአምራትህን እንዲያዩ የሚልና፣ ራሱን መግለጥ የሚፈልግ ሰው ተሰውሮ መመላለስ እንደሌለበት የሚል ነበረ፡፡ ዮሐንስ የገዛ ወንድሞቹ በዚያን ሰዓት በኢየሱስ የሚያምኑ እንዳልሆኑ ነው የተናገረው፡፡
3. በዚህ ክፍል የሚያነጻጽረው ራሱንና እነርሱን ማለትም ወንድሞቹን ነው፡፡ ጊዜን አስመልክቶ በሁለቱ መሃል ያለው ልዩነት፤ ለኢየሱስ ትክክለኛ ጊዜ የሚባል ሲኖር ለወንድሞቹ ግን የትኛውም ጊዜ ከየትኛው ልዩነት የለውም፤ ይህም ማለት በፈለጉበት ሰዓት ወደ ይሁዳ ቢሄዱ የሚገጥማቸው ችግር አይኖርም፡፡
4. ቁ5 እንደሚነግረን ወንድሞቹ ከዓለም ስለሆኑና ዓለም ሊጠላቸው አይችልም፤ ኢየሱስ ግን የዓለምን ክፋትና ከዚህም ክፋታቸው ደግሞ መመለስ እንደሚኖርባቸው በግልጽ ስለሚነግራቸው እርሱን ይጠሉታል፤ ስለዚህም ያለጊዜው ወደ ይሁዳ ቢሄድ የማያስፈልግ ችግር ውስጥ ይገባል ማለት ነው፡፡
5. ኢየሱስ ወደ በአሉ የሄደው ወንድሞቹ ከሄዱ በኋላ ነው፡፡ ሌላ ስለ አካሄዱ የምናነበው ነገር፤ ሲሄድም በግልጽ ሳይሆን በስውር እንደሆነ እንረዳለን፡፡
6. በሰዎቹ መሃል ይካሄድ የነበረው አንድ ነገር ‹‹ጉምጉምታ›› ነበረ፡፡ ኢየሱስን አስመልክቶ ደግሞ አንዳንዶቹ ሰዎች ‹‹ደግ ሰው ነው›› የሚል አመለካከት ሲኖራቸው፤ ሌሎቹ ደግሞ ‹‹የለም ህዝቡን የሚያስት ሰው ነው›› የሚል አመለካከትን ይሰነዝሩ ነበረ፡፡
7. አይሁድን ያስገረመው ነገር የኢየሱስ ሳይማር መጻህፍትን የማወቅ ነገር ነበረ፡፡ ትምህርቱ ከራሱ ሳይሆን ከላከው እንደሆነ፣ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ማድረግ የሚፈልግ ሰው የኢየሱስ ትምህርት ከእግዚአብሄር ወይም ከራሱ ከየሱስ መሆኑን ያውቃል፡፡
8. ትምህርቱን ከመቃወም አልፈው እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ‹‹ኢጋንንት ያደረብህ›› ሲሉት እናነባለን፡፡ እነዚህ ሰዎች ብዙ የተለያየ ምክንያት ይስጡ እንጂ፤ ኢየሱስ ስለተቆጡና ስለተናደዱበት ምክንያት ለራሳቸው ሲነግራቸው፤ የሰውን ሁለንተና በሰንበት ስለፈወሰ መሆኑን እንረዳለን፡፡
9. ይህ የኢየሱስ ድርጊት እርሱ ከተወሰነለት ጊዜ ውጭ መሞት እንደሌለበት እንደተረዳና በሁኔታዎች ውስጥም ጥበብን ይጠቀም እንደነበረ እንረዳለን፡፡ ከዚህ አድራጎቱ መማር የምንችለው፤ ራሳችንን ለማያስፈልግ አደጋ አሳልፈን መስጠት መንፈሳዊነት እንዳልሆነና በጥበብ መመላለስ ለኢየሱስ ካስፈለገ ለእኛ የበለጠ እንደሚያስፈልገን እንማራለን፡፡

# ጥናት አስራ ዘጠኝ ዮሐንስ 7፡25-36 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ቁ25 እንደሚናገረው ጥያቄያቸው የነበረው፤ ሊገድሉት እየተፈለገ ያለሰው እንደዚህ እንዴት በግልጽ ሊያስተምር ይችላል የሚል ነበረ፡፡ ለራሳቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ፤ ምናልባትም ባለስልጣናቱ ራሳቸው ክርስቶስ መሆኑን አምነው ተቀብለውት ይሆናል የሚል ነው፡፡
2. እውቀት የሚለው ቃል በተለያዩ መንገዶች ቢያንስ ስድስት ጊዜ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህ ከስድስቱ በሙሉ ከክርስቶስ ጋራ በተያያዘ የተነገሩ ናቸው፡፡
3. በዚህ ክፍል ስለጊዜ የሚናገረው፤ በእግዚአብሄር እቅድ ክርስቶስ በሚገድሉት እጅ እንዲገባና በመስቀል ሊሞት የተወሰነበት ቀን ማለቱ ነው፡፡ ጌታ በትምህርቱ ያገኛቸው ሁለት ምላሾች አንዱ ሊይዙትና ሊያስሩት የሚፈልጉ ሲኖሩ፤ ሌሎቹ ደግሞ ቁ31 ላይ በእርሱ አምነው የሚላቸው ሰዎች ናቸው፡፡
4. ክርስቶስ የተባለው ሲመጣ ይህ ሰው ከሚያደርገው ተአምራቶች የበለጠ የበለጠ ስለማያደርግ ይህ ሰው ክርስቶስ መሆን አለበት የሚለውን ሳይሆን አይቀርም፡፡ ፈሪሳውያኑ ኢየሱስ እንዲያዝ የወሰኑት ምናልባትም የህዝቡ አመለካከት በዚህ ከቀጠለ ብዙዎች በእርሱ ያምናሉ በሚል ፍርሃት ነው፡፡
5. እነርሱን እያስተማረ የሚቆየውና ጥቂት ጊዜ የሚለው በመስቀል እስከሚሞትበት ያለውን ጊዜ ነው፡፡ በሞት እንደሚለያቸው እየነገራቸው ተመልሶ በቁ34 ላይ ወደላከኝ እሄዳለሁ ማለቱ መቃብር ይዞ ሊያስቀረው እንደማይችል እርግጠኛነቱን ለኛም ያረጋግጥልናል፡፡
6. ለአይሁድ ጥያቄ የሆነባቸው ነገር ‹‹ትፈልጉኛላችሁ ግን አታገኙኝም›› የሚለውና ‹‹እኔ ወዳለሁበት ልትመጡ አትችሉም›› ያላቸው አነጋገሮቹ ናቸው፡፡ ሁለቱ ያሰቡት የተራራቀ ሃሳብ ነው፤ ምክንያቱም እሱ የሚያወራው ስለሞቱና ተነስቶ ወዳባቱ ስለመሄዱ ሲሆን፤ እነሱ ደግሞ ቦታ የመለወጥ ነገር ነው፡፡ ሁለቱ በአመለካከት የሚራራቁት እነሱ የሚያስቡት ምድራዊውን ሲሆን እሱ ግን የመናገራቸው ሰማያዊ ነገሮችን ስለሆነ ነው፡፡
7. ሰዎቹ የሰነዘሯቸው ሁለት ሃሳቦች የመጀመሪያው ይህ ሰው ከየት እንደሆነ እኛ እናውቃለን ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ክርስቶስ ሲመጣ ከየት እንደሆነ ማንም አያውቅም የሚሉት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በሥጋ አነጋገር ትክክል ናቸው ሊባል ሲችል፤ በትክክል ከየት እንደመጣ ግን ከሰማይ መጣሁ ስለሚል አላወቁትም፤ ሁለተኛው ግን ክርስቶስ የት እንደሚወለድ ግልጽ ሆኖ ስለተነገረ እነሱ ማንም አያውቅም ያሉት ስህተት ነው፡፡ ፈሪሳውያኑ ህዝቡ የህግ እውቀት እንደሌለው ይናገራሉ፡፡

# ጥናት ሃያ ዮሐንስ 7፡37-53 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዮሐ 7፡2 ላይ የአይሁድ የዳስ በዓል እንደነበረ ይነግረናል፡፡ በሰባተኛው ቀን ሲሆን፤ ዮሐንስ ይህንን ቀን ታላቁ ቀን በማለት ነው የሚናገረው፡፡
2. ሀ) ‹‹ማንም›› ጥሪው ለማንም ሰው እንደሆነ ለ) ‹‹የተጠማ›› ጥሪው ለተጠሙ ሰዎች ብቻ መሆኑ ሐ) ‹‹ወደ እኔ›› ጠሪው ኢየሱስ እንደሆነ መ) ‹‹ይምጣ›› ወደየሱስ መምጣት እንደሚጠይቅና ሠ) ‹‹ይጠጣ›› የሱስ የሚሰጠውን ውሃ መጠጣት እንደሚያስፈልግ፡፡
3. ቁ39 እንደሚነግረን ውሃ እያለ በቁ37 የተናገረው አማኞች ስለሚቀበሉት መንፈስ ነበረ፡፡ ውሃ ለሰዎች ጥማት እርካታን እንደሚሰጥ፤ ደግሞም የተዘራ ዘር እንዲበቅልና እንዲያፈራ እንደሚያደርግ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም በአማኝ ህይወት ውስጥ ገብቶ እርካታንና ፍሬያማነትን እንዲሁም ለተጠማው ዓለም  የሚተርፍ በረከት ሊኖረው እንደሚገባ ያመለክተናል፡፡ ዮሐ 4፡14 ተመልከት፡፡
4. ቁ43 እንደሚነግረን ‹‹በኢየሱስ ምክንያት በህዝቡ መካከል መለያየት ሆነ›› ይለናል፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሶስት አይነት አመለካከቶችን እናያለን፡ እነዚህም ‹‹ነብዩ ነው›› ‹‹ክርስቶስ ነው›› የሚሉና ሌሎቹ ደግሞ ቃል በቃል ባይሉትም ኢየሱስ እነርሱ ያሰቧቸውን ሁኔታዎች ያሟላል ብለው ስላላመኑ ክርስቶስ አይደለም ብለው የደመደሙ ደግሞ ነበሩ፡፡
5. ጠባቂዎቹ የተላኩት ኢየሱስን ይዘው እንዲያመጡት ነበረ፡፡ ኢየሱስን ይዘው ያላመጡበት ምክንያት ኢየሱስ የተናገራቸውን ንግግሮቹን በመስማት ትምህርቱ ከዚህ በፊት ሰምተው የሚያውቁት አይነት ስላልነበረ ‹‹እንደዚህ ሰው ከቶ ማንም ተናግሮ አያውቅም›› ብለው ነው የመለሱት፡፡ ፈሪሳውያኑ ይህንን የጠባቂዎቹን አመለካከት እንደተታለሉና እንደተሞኙ አድርገው ነው የቆጠሯቸው፡፡
6. እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄርን ምስጢር መረዳት የምንችለው እኛ የተማርነውና ጥበበኞቹ ነን እንጂ ይህ ተራ ህዝብ ወደመሩት የሚሄድ በእነርሱ አመለካከት የተረገመ ህዝብ ነው፡፡ በማቴ 11፡25 ላይ ግን ኢየሱስ እግዚአብሄርን ሲያመሰግን የሚታየው ይህ ሰማያዊ ምስጢር የተገለጠው ምንም አያውቁም ለተባሉና ላልተማሩ ሲሆን፤ አዋቂ ነን ለሚሉ ደግሞ እንደተሰወረና ፈሪሳውያኑ ከሚያስቡት ተቃራኒ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡
7. ኒቆዲሞስ አስመልክቶ የምናየው ከዚህ ቀደም ወደ ኢየሱስ ሄዶ እንደነበረና አሁንም ደግሞ ከህግ አስተማሪዎቹ መሃል አንዱ እንደሆነ እናነባለን፡፡ እንደ ኒቆዲሞስ አነጋገር በአንድ ሰው ላይ ለመፍረድ አስቀድሞ ቃሉን መስማት፤ በተጨማሪም ሥራውን መመዘንና መረዳት እንደሚያስፈልግ ይናገራል፡፡ ኢየሱስ ትምህርቱም ሆነ መልካምን እየሰራ፣ በሽተኞችን እየፈወሰ፣ እውርን ማብራቱ የሚያስፈርድበት እንዳልሆነ ሁሉም ያውቁታል፡፡
8. በቁ52 ላይ እንደምናነበው እነዚህ ሰዎች የንቀት ንግግር ሲናገሩና፤ መጻህፍትን እንደማያውቅና ገና መመርመር የሚያስፈልገው ሰው መሆኑን በንቀት ቋንቋ ሲናገሩት ይታያል፡፡ ይህ ሰው ብቻውን ሆኖ ብዙዎች ቢሆኑም ለእውነት መቆሙ እኛም በጌታ ጸጋ ከእውነት ጋራ መቆምን መለማመድ እንደሚኖርብን እማራለሁ፡፡

# ጥናት ሃያ አንድ ዮሐንስ 8፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በክፍሉ ውስጥ የሚታዩት ተዋናኞች የህግ መምህራንና ፈሪሳውያን፣ ኢየሱስ፣ ከእርሱ ለመማር የተቀመጠው ህዝብ፣ በዝሙት የተያዘችው ሴት፡፡
2. ህዝቡ የተገኙት ከኢየሱስ ለመማር፣ ኢየሱስ ለማስተማርና፣ ፈሪሳውያኑ ደግሞ ለክስና ኢየሱስን ለማጥመድ ማለትም የራሳቸውን አጀንዳ ለመፈጸም ነበረ የተገኙት፡፡ እያንዳንዱ የራሱን መልስ ይስጥበት፡፡ ሰዎች ወደቤቱ ሲመጡ፤ ከእርሱ ለመማር፣ ልምድ ስለሆነ፣ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት፣ ቤተ ሰቦቻቸው ስለሚሄዱና ለመሳሰሉት ምክንያቶች ይሄዳሉ፡፡
3. በሃፍረት እንደምትሞላና ምድር ብትውጣት ትመኛለች ብዬ አስባለሁ፡፡ ከሳሾችዋ ግን ስለስዋ ስሜት ይገዳቸዋል ብዬ አላስብም፤ ምክንያቱም የእነርሱ አንዱና ልባቸውን ያሳወረው አጀንዳቸው ኢየሱስን አጥምዶ ለፍርድ ማብቃት ስለሆነ ነው፡፡
4. ለጥያቄያቸው አጭርና ቀላሉ መልስ ህግ እንደሚለው አድርጉ ማለት ነበረ፡፡ ለእግዚአብሄር ህግ ተቆርቁረው እንዳልሆነ በቁ6 ላይ ዮሐንስ ግልጽ አድርጎ አስፍሮልናል፡፡
5. ኢየሱስን ልክ ዳንኤልን በአምላኩ ህግ ብቻ እንጂ ሌላ ስህተት ሊያገኙበት እንዳልቻሉ፤ ኢየሱስንም በሃጥያት ለመክሰስ ወይም ለመፈተን ስለማይችሉ በእርሱም ላይ መምጣት የሚችሉት በአምላኩ ህግ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡
6. ኢየሱስ የመለሰላቸው ‹‹ከእናንተ ሃጥያት የሌለበት እርሱ አስቀድሞ ድንጋይ ይወርውርባት›› የሚል ነው፡፡
7. መልሱን እንደሰሙ እያንዳንዳቸው ሹሉክ ብለው እንደ ወጡና ሁለቱ ብቻ እንደቀሩ ቁ9 ይነግረናል፡፡ አንዳቸውም ድንጋይ ለመወርወር ድፍረት ያጡበት ምክንያት ውስጣቸውን ሲመለከቱ ማናቸውም ቢሆኑ ያለሃጥያት አለመሆናቸው ስለገባቸው ነው፡፡ ከኢየሱስ ድርጊትና አነጋገር ልንማር የምንችለው ሰዎችን በምህረት ማቅናትና ሌላው ደግሞ በራሳችን ዓይን ውስጥ የተጋደመውን ምሰሶ ማስወገድ የሚሉትን ሁለት ሃሳቦች መማር ይቻላል፡፡
8. ኢየሱስ ያስተላለፋቸው ሁለት ሃሳቦች፡ የመጀመሪያው እርሱም እንደማይፈርድባትና ሁለተኛው ደግሞ ደግማ ሃጥያት እንዳትሰራ ማስጠንቀቅ ነበሩ፡፡ ለማንኛውም ሰው ኢየሱስ ምህረትን በመስጠት፤ ምህረትን ከሰጠ በኋላ ደግሞ ከሃጥያት መለየት እንደሚገባም የሚናገር አምላክ ነው፡፡

# ጥናት ሃያ ሁለት ዮሐንስ 8፡12-30 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ፈሪሳወያኑ ተቀባይነት እንደሌለው የሚናገሩት ‹‹እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ›› የሚለውን ሃሳብ ነው፡፡ እርሱን የሚከተል ሰው የህይወት ብርሃን እንደሚሆንለትና በጨለማ እንደማይመላለስ ነው ቃል የገባው፡፡
2. ከየት እንደመጣና ወዴት እንደሚሄድ ማወቁና እነዚህ ከሳሾቹ ግን እርሱ ከየት እንደመጣ ወዴትም እንደሚሄድ አያውቁም፡፡ ዮሐ 7፡27 ሰዎቹ ኢየሱስ ከየት እንደሆነ እናውቃለን የሚል አመለካከት እንዳላቸው ነው ይህ ክፍል የሚያስረዳን፡፡ ዮሐ 7፡36 እና 8፡22 ደግሞ የሚያስረዱን ኢየሱስ የሚሄድበትን እነዚህ ሰዎች እንደማያውቁ ከሰዎቹ አፍ የሚያረጋግጥልን እውነት ያሳየናል፡፡
3. ብርሃንን አስመልክቶ፡ ወንድምን በመውደድ 1ኛ ዮሐ 2፡10 ሥራ በብርሃን እንደሚሰራ ዮሐ 9፡4 ልብሳችን የብርሃን ጦር እቃ ነው ሮሜ 13፡12 አረማመዳችን በብርሃን ኤፌ 5፡8 የመሳሰሉትን ሲጨምር፤ ጨለማ ደግሞ ጥላቻ 1ዮሐ 2፡10 በጨለማ እየተመላለሱ ከየሱስ ጋራ ህብረት የለም 1ኛ ዮሐ 1፡6
4. በማንም አልፈርድም ያለው ኢየሱስ ሰዎችን ለማዳን እንጂ በሰዎች ለመፍረድ ወይም ለመኮነን አልመጣምና በዚህ በኩል ያለውን ሲያሳየን ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን ፍርድ የሚለው ስለሰዎች ህይወት፣ አስተሳሰብ፣ ድርጊትና የልብ ሃሳባቸውን በትክክል ሳይሳሳት ሊፈርድ ማለትም ትክክል ናችሁ ወይም አይደላችሁም ማለት የሚችል እንደሆነ መናገሩ ነው፡፡ ቁ26 መመልከት ይረዳል፡፡
5. በዚህ ቁጥር ላይ ጥያቄያቸው ‹‹አባትህ የት ነው?›› የሚል ሲሆን ኢየሱስ ለጥያቄው ቀጥተኛ የሆነ መልስ ሰጥቷል ብዬ አላምንም፤ ምክንያቱም እነርሱ የጠየቁት ያለበትን ሥፍራ ሲሆን እርሱ እየመለሰ ያለው ግን አባቱን የማወቅ ያለማወቃቸውን ጉዳይ አስመልክቶ ነው፡፡
6. እነዚህ ሰዎች በብዙ መንገድ ኢየሱስን አምነው ህይወት እንዲሆንላቸው የተነገራቸው ሲሆኑ፤ እግዚአብሄር ለመዳን እንዲሆንላቸው የሰጣቸውን እድል ሊጠቀሙበት አለመፈለጋቸው በሃጥያታቸው እንዲሞቱ ያደርጋቸዋል፤ ይህም ማለት መሲሁን ሳይቀበሉ ከነሃጥያት መሞት ኢየሱስ ወደሚሄድበት መሄድ እንዳይችሉ ይከለክላቸዋል ማለት ነው፡፡ በቁ23-24 ግልጽ አድርጎ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ካላመኑ በሃጥያታቸው እንደሚሞቱ ነገራቸው፡፡
7. ለመሆኑ አንተ ማንነህ? የሚል ነው ጥያቄያቸው፡፡ ኢየሱስ ደግሞ በአጭሩ እኔ አስቀድሜም የነገርኳችሁ እርሱ ነኝ ይላቸዋል፡፡ ‹‹እስካሁን የነገርኳችሁ›› ሲል ኢየሱስ ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ እንደነገራቸው ያስረዳናል፡፡
8. የላከው አብ ከእርሱ ጋራ እንዳለ ነው የሚናገረው፡፡ ሁልጊዜ ከእርሱ ጋራ የመሆንበትም ምክንያት፤ ኢየሱስ ምንጊዜም የሚያደርገው አብን የሚያስደስተውን ነገር እየመረመረና እየመረጠ ስለሆነ ነው፡፡

## ጥናት ሃያ ሶስት ዮሐንስ 8፡31-59 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ውይይቱ የተካሄደው በኢየሱስ ባመኑት አይሁድና በኢየሱስ መሃል ነው፡፡ በዚህ ቦታ ለነዚህ ሰዎች ለዎች ለመዋጥ ወይም ለመቀበል ያስቸገራቸው ትምህርት እውነትን በማወቅ ነጻነት እንዳለ የተናገራቸው ነገር ነው፡፡
2. አይሁዶቹ ባርነት ሲባል የሚያስቡት በስጋ ለሰው ባሪያ መሆን የሚለውን ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን በዚህ ቦታ ባርነት ሲል የመንፈስ ባርነትን ሆኖ ለሃጥያት ተገዢና ባሪያ መሆንን ነው፡፡ በዚህ ቦታ ነጻ የሚያወጣው እውነት የሆነው ራሱ ኢየሱስ ነው፡፡
3. በቁ37 ላይ ያመነው በሥጋ ያላቸውን የአብርሃም ልጅነት ሲሆን፤ በቁ39 ላይ ግን የሚክደው መንፈሳዊ የአብርሃም ልጅነት እንደሌላቸው ነው፡፡ ክፍሉን ያነበበ ማንም ሰው እነዚህ ሰዎች ያመኑ ናቸው ወደሚለው ሃሳብ የሚደርስ አይመስለኝም፤ ምክንያቱም አልፈው ተርፈው ኢየሱስን ኢጋንንት አለብህ በማለት እንደከሰሱት ይታያል፡፡
4. በመንፈስ የአብርሃም ልጆች አለመሆናቸውን፣ የሃጥያት በሪያዎች መሆናቸውን፣ የዲያቢሎስ ልጆች እንደሆኑ፡፡ ኢየሱስ ይህንን ሁሉ ማለት የቻለው ከድርጊቶቻቸውበመነሳት ነው፡፡
5. ሁለቱን የሚለየው አንድ ነገር የኢየሱስ እውነተኛነትና የዲያቢሎስ የውሸት አባት መሆኑ ነው፡፡ በክፍሉ መሰረት ኢየሱስ ሊከሰስ የማይችልበት ነገር ሃጥያት ነው፡፡
6. በዚህ ቦታ ውይይቱ ያተኮረው በኢየሱስ ውስጥ ኢጋንንት መኖሩን ለማረጋገጥ በመሞከር ላይ ነው፡፡ ለአይሁዶቹ በኢየሱስ ውስጥ ኢጋንንት ለመኖሩ እንደማረጋገጫ አድርገው የወሰዱት ‹‹ማንም ቃሌን ቢጠብቅ ሞትን ፈጽሞ አያይም›› የሚለውን አነጋገሩ ለነርሱ ማረጋገጫ ሆኖ ነው ያገኙት፡፡
7. የተዋረደው በሰዎች ሲሆን፤ የተከበረው ግን በአባቱ ነው፡፡ በሰዎቹ መዋረዱ ምንም ስሜት እንዳልሰጠው ይታያል፤ ምክንያቱም እርሱ በመጀመሪያውም ቁ50 እንደሚናገር ለክብር ፍለጋ የመጣ ሳይሆን አባቱን ለማክበር የመጣ ነው፡፡
8. እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄር ልጆች ላለመሆናቸው ኢየሱስ ያቀረበው መረጃ በልባቸው ውስጥ ብቻ ሳይሆን አልፎም እርሱን ለመግደል የሚያደርጉት ሙከራ ጥላቻቸውን ስለሚያሳይ ይህ የዲያቢሎስ ልጅነትን እንጂ የእግዚአብሄር ልጅነትን እንደማያመለክት ነግሯቸዋል፡፡

# ጥናት ሃያ አራት ዮሐንስ 9፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ደቀመዛሙርቱ የጠየቁት ጥያቄ ‹‹አይነ ስውር ሆኖ እንዲወለድ ሃጥያት የሰራ ማን ነው? እርሱ ራሱ ወይስ ወላጆቹ?›› የሚል ነበረ፡፡ ይህ ጥያቄ በተለይም በአይሁድ ህብረተሰብ ሰው አካለ ስንኩል ነው ማለት ሁልጊዜ ከሃጥያት ጋራ ተያይዞ ስለሚታይ ደቀመዛሙርቱም ከዚያ አስተሳሰብ ውስጥ ገና ስላልወጡ ነው ይህ ጥያቄ ሊነሳ የቻለው፡፡
2. ኢየሱስ ለጥያቄአቸው የመለሰው እርሱ ራሱ ወይም ወላጆቹ ስለሰሩት ሃጥያት እንዳልሆነና ነገር ግን የእግዚአብሄር ሥራ በህይወቱ እንዲገለጥ እንደሆነ ነው የነገራቸው፡፡ ኢየሱስ ይህንን ማለቱ ሰዎች በታመሙ ቁጥር ለእግዚአብሄር ክብር ነው የታመሙት እንድንል ሳይሆን፤ የዚህ ሰው እውርነት ለተናገረው ምክንያት እንደሆነ፤ ሌሎችም እግዚአብሄር በዚህ መንገድ ሊጠቀምባቸው ያዘጋጃቸው ሊኖሩ እንደሚችሉም አያጠራጥርም፡፡ ወደፍርድ ከመሄድ በፊት ኢየሱስን ጠይቆ መረዳጥ ይጠቅማል፡፡
3. ኢየሱስ በምድር ላይ እንትፍ ብሎ ጭቃ እንዳበጀና የሰውየውን ዓይን በመቀባት ሰውየውን ሄዶ በሰሌሆም መጠመቂያ እንዲታጠብ ሲያዘው እንመለከታለን፡፡ በኢየሱስ የተላከው እውር ሰው ደግሞ እንደተባለው ሄዶ እንደታጠበና እያየ እንደመጣ ይታያል፡፡ ንእማን እንዲታጠብ ሲታዘዝ የዮርዳኖስን ውሃ ከአገሩ ወንዝ ጋራ ማወዳደር እንደጀመረ ይህ ሰው ሳይጠይቅ የታዘዘውን ማድረጉ ይለየዋል፡፡
4. አንዳንዶች ‹‹እርሱ ነው›› ይላሉ፤ ሌሎች ‹‹ይመስለዋል እንጂ እርሱ አይደለም›› ሲሉ፤ እርሱ ደግሞ ‹‹እኔው ነኝ›› በማለት ይናራል፡፡ የጎረቤቶቹ ጥያቄ ‹‹አይኖችህ እንዴት ተከፈቱ?›› የሚል ነበረ፡፡ ለጥያቄያቸው ሰውየው የመለሰው፤ ኢየሱስ አይኔን ጭቃ ቀባኝ፣ በሰሌሆም እንድታጠብ ነገረኝ፣ ሄጄ ታየብሁ፣ ማየትም ቻልኩ፡፡
5. እኔ ሲመስለኝ ይህ ሰው ኢየሱስ ያደረገውን ሁሉ ሲያደርግበት ዓይኖቹ የማያዩ እውር ስለነበረ በዚያ በአጠገቡም ቆሞ ቢሆን እንኳን ሊለየው እንደማይችል ይመስለኛል፡፡ ሰዎቹ ወደ ፈሪሳውያን የወሰዱበት ምክንያት ኢየሱስ ሰውየውን የፈወሰበት ቀን ሰንበት ስለነበረ ነው፡፡ በቁ14 ላይ ያሉት የመጀመሪያው በሰንበት ጭቃ መጠፍጠፍ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ አይን መከፈት ናቸው፡፡
6. በዚህ ስፍራ ደግሞ ለሃይማኖት መሪዎች ማለትም ለፈሪሳውያን ኢየሱስ የሰራውን እንዲናገር በር ተከፈተለት፡፡ ለማንም ቢሆን ምስክርነቱ ጭቃ እንደቀባው፣ ታጠብ ብሎት እንደታጠበና፣ አሁን ደግሞ እንደሚያይ ነው፡፡
7. በፈሪሳውያን መሃል አለመስማማት ሲፈጠር ይታያል፡፡ አንዳንዶቹ ሰንበትን ስለማያከብር ሃጥያተኛ ነው ወይም ደግሞ ከእግዚአብሄር ሊሆን አይችልም ሲሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ሃጥያተኛ እንደዚህ ያለ ተአምራዊ ምልክት ሊያደርግ አይችልም የሚሉ ነበሩ፡፡
8. መልሱ ‹‹እርሱ ነብይ ነው›› የሚል ነው፡፡ ወረድ ብለን ፈሪሳውያኑ እርሱን ሃጥያተኛ ለማድረግ የወሰዷቸውን መንገዶች ሁሉ ስመለከት የጠበቁት ነገር እነርሱን በመፍራት የማስተባበያ ወይም ሰንበትን ባለማክበሩ ሃጥያተኛ አድርጎ እንዲናገር ይመስለኛል፡፡

# ጥናት ሃያ አምስት ዮሐንስ 9፡18-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ወላጆቹ እንዲጠሩ ያስፈለገበት ምክንያት አይሁድ ሰውየው እውነት አይነስውር እንደነበረና አሁን እንዳየ ለማረጋገጥ ነበረ፡፡ ወላጆቹ የተጠየቁት አንደኛው እውር የነበረው ልጃችሁ ይህ ነው ወይ? ሁለተኛው ደግሞ አሁን እንዴት ሊያይ ቻለ የሚሉት ናቸው፡፡
2. የሚያውቋቸው ሁለት ነገሮች፤ ልጃቸው መሆኑንና አይነስውር ሆኖ መወለዱን ሲሆን፤ የማያውቋቸው ደግሞ አሁን እንዴት ማየት እንደቻለና አይኖቹን ማን እንደከፈተለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የነገሯቸው እርሱ ስለራሱ መናገር ስለሚችል እርሱን ራሱን እንዲጠይቁት ነው፡፡
3. ወላጆቹ እንደዚያ ያሉበት ምክንያት ከምኩራብ እንዳይባረሩ በፍርሃት እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ስለወላጆቹ ከክፍሉ መረዳት የምችለው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ አምነው የተቀበሉና ያንን ለመናገር ግን ፍርሃት እንደነበራቸው ኣያለሁ፡፡ በእኔ አስተሳሰብ ሰዎቹ የተናገሩት ነገር በሙሉ ትክክል እንደሆነና ድርጊታቸው ጥበብ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡
4. አይሁድ ደግመው የጠየቁት ነገር ምን እንዳደረገለትና እንዴትስ አይኑን እንደከፈተለት ነው፡፡ ከሰውጠው አመላለስ ያየሁት አንደኛው የጥያቄው ብዛት እንዳሰለቸውና፤ ሌላው ደግሞ እርሱ በልቡ ያዳነው ሰው ደቀ መዝሙር ለመሆን የወሰነ ይመስላል፡፡
5. ለጥያቄው ያገኘው መልስ በመጀመሪያ የስድብ ናዳ በማውረድ የእነርሱ ደቀ መዝሙርነት ለሙሴ መሆኑን በማረጋገጥ ነው የመለሱለት፡፡
6. በነዚህ አይሁዶች አይን ኢየሱስ ሃጥያተኛ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ ይህ ሰው የተጠየቀው ከአይሁዶቹ ጋራ እንዲስማማና ኢየሱስ ሃጥያተኛ ነው እንዲል፤ ይህንንም በማድረጉ እግዚአብሄርን እንደሚያከብር ነው የተነገረው፡፡
7. በመጀመሪያ ደረጃ የኢየሱስን ሃጥያተኛነት እንደማያውቅ ማለትም እንደማይስማማ ነግሮ በተጨማሪ ደግሞ እርሱ እውር እንደነበረ አሁን ግን እንደሚያይ ያረጋግጥላቸዋል፡፡ ከጥያቄያቸው በስተኋላ የኢየሱስን ማንነት ማስተባበል እንደሆነ ነው የሚገባኝ፡፡ ስለ ኢየሱስ ማንነትና እንዲሁም ስለደህንነትህ አዋቂዎች ነን የሚሉ ሰዎች በጥያቄ ውርጅብኝ አጣድፈውህ ያውቃሉ ወይ? የእነርሱን ያህል እውቀት ላይኖርህ ይችላል ሆኖም አንድ መናገር የምትችለው ነገር ቢኖር፡ ሃጥያተኛ እንደ ነበርክ ዛሬ ግን ይቅርታን ተቀብለህ በሰላም እንደምትመላለስ መናገር ትችላለህ፡፡

# ጥናት ሃያ ስድስት ዮሐንስ 9፡30-41 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህንን ሰው ያስደነቀው አንድ ነገር አይኑን የከፈተለት ሰው ከየት እንደመጣ አለማወቃቸው ነው፡፡ ‹‹ይሁን እንጂ እርሱ አይኖቼን ከፈተልኝ‹‹ በማለት ዋናው ነገር ያ እንደሆነ ያሳስባቸዋል፡፡
2. የነዚህ ሰዎች አለማወቅ ያስገረመው ምክንያት ለእኔ እንደሚገባኝ ሰዎቹ በ9፡13 ላይ ስናነብ የህግ አስተማሪዎች የሆኑ ፈሪሳውያን ሲሆኑ የዚህን ሰው ከእግዚአብሄር መሆን ማወቅ እንደነበረባቸው ስለገመተ ይመስለኛል፡፡
3. የመጀመሪያው እነርሱ ትምህርታዊ በሆነ መንገድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከልምድ በመነሳት ነው፡፡ በሰውየው አነጋገር እግዚአብሄር የሚሰማው የሚፈራውንና ፈቃዱን የሚያደርገውን ሰው ነው፡፡
4. ኢየሱስ እግዚአብሄርን ይፈራል (ቁ31)፣ ኢየሱስ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ያደርጋል (ቁ31)፣ ኢየሱስ ከእግዚአብሄር የተላከ ወይም የመጣ ነው (ቁ33) የሚሉት ናቸው፡፡
5. ኢየሱስ የጠየቀው ‹‹በሰው ልጅ ታምናለህን?›› የሚል ሲሆን የሰውየው መልስ ደግሞ ‹‹ጌታዬ፤ አምንበት ዘንድ እርሱ ማንነው?›› የሚል ነበረ፡፡
6. ኢየሱስ ማንነቱን በገለጠለት ጊዜ ይህ ሰው ያደረገው በኢየሱስ እንደሚያምን ተናግሮ እንደሰገደለት እንመለከታለን፡፡ ኢየሱስ የመጣሁት እውሮች እንዲያዩ፤ የሚያዩ እንዲታወሩ ለፍርድ እንደመጣ ነው፡፡
7. የኢየሱስ ንግግር ያስከተለው ጥያቄ፤ ‹‹ምን ማለትህ ነው ታዲያ እኛም እውሮች መሆናችን ነው?›› አሉት ይላል፡፡ እርሱ የመለሰው መልስ ‹‹እውሮች ብትሆኑ ሃጥያት ባልሆነባችሁ ነበር፤ አሁን ግን እናያለን ስለምትሉ ሃጥያታችሁ እንዳለ ይኖራል›› የሚል ነው፡፡ እውር ሆነው እያሉ እውርነትን ያለመቀበል፤ ማለትም እርዳታ የሚያስፈልገን ሆነን እያለን እርዳታ አያስፈልገኝም ማለት ትልቅ በሽታ ነው፡፡
8. እነዚህን ሰዎች መቀበል የተቸገሩት ነገር ይህ ሰው በመጀመሪያ ደረጃ እውር መሆኑ በሃጥያት እንደተወለደ አድርገው ማየታቸውና በተጨማሪም ደግሞ እነርሱ የሙሴን ህግ አጥርተው እንደሚያውቁ አድርገው ስለሚያምኑ ከእርሱ መስማትን በጭራሽ በንቀት ነው ያዩት፡፡

# ጥናት ሃያ ሰባት ዮሐንስ 10፡1-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቦታ የሚያወዳድረው ሌባና ነጣቂ እና እውነተኛን የበጎች እረኛ ነው፡፡ እረኛ የሚገባው በበር ነው፣ ለእውነተኛ እረኛ ጠባቂው ይከፍትለታል፣ በጎቹ ድምጹን ይሰማሉ፣ በጎቹን በየስማቸው እየጠራ ያስማራቸዋል፣ ፊት ፊታቸው ይሄዳል፡፡
2. ድምጽ ማወቅና አለማወቅ ነው ለመከተልም ሆነ ላለመከተል ምክንያት እንደሚሆናቸው የምናነበው፡፡ በጎቹ ይህንን እንግዳ አለመከተል ብቻ ሳይሆን ከእርሱ እንደሚሸሹም ነው የተነገረው፡፡
3. በቁ6 ላይ እንደምናነበው ከላይ የነገራቸውን ምሳሌ ሊየስተውሉት ስላልቻሉ ነው ተከታዩን መናገር ያስፈለገው፡፡ ራሱን ኢየሱስ እንደ በጎች በር አድርጎ ነው ያቀረበው፡፡ በኢየሱስ በኩል የሚገባ ቁ9 እንደሚናገረው፤ ይድናል፣ ይገባል፣ ይወጣል፣ መሰማሪያም ያገኛል፡፡
4. ኢየሱስ ራሱን የሚያወዳድረው ከሌባው ጋራ ነው፡፡ ሌባው የሚመጣው፤ ሊሰርቅ፣ ሊገድል፣ ሊያጠፋ ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን የመጣው ህይወት ሊሰጥና ሊያትረፈረፍልን ነው፡፡
5. ኢየሱስ ራሱን እንደ መልካም እረኛ አድርጎ ነው የሚናገረው፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ራሱን ሲያነጻጽር የሚታየው ከተቀጣሪ እረኛ ጋራ ነው፡፡ ኢየሱስ ህይወቱን ለበጎቹ አሳልፎ ይሰጣል፤ ተቀያሪው እረኛ ግን በጎቹ የእርሱ ስላልሆኑ ተኩላ ሲመጣ ጥሏቸው ይሸሻል፡፡ ከተኩላ ጋራ ለመጋፈጥ የማይፈልግበት ምክንያት እርሱ ተቀጣሪ ስለሆነና በጎቹ የእርሱ ስላልሆኑ ለእነርሱ ደንታ ስለሌለው ነው፡፡
6. በበጎችና በእረኞቻቸው መሃል ያለው የጋራ ነገር መተዋወቅ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህ አይነቱን መተዋወቅ ሲያነጻጽር የሚታየው ከአብና ከወልድ መተዋወቅ ጋራ ነው፡፡ በአንድ በኩል ብቻ ሳይሆን በሁለቱም ዘንድ የመተዋወቅ ነገር መኖሩ ሁለቱም እርስ በእርስ የመፈላለግን ነገር ሲያሳየኝ፤ በተለይም በእኔ በኩል እርሱን ለማወቅ የበለጠ ጥረት እንዳሳይ ያሳስበኛል፡፡
7. በቁ16 ላይ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ገና በእርሱ ስላላመኑትና ነገር ግን ወደፊት ስለሚያምኑት ሰዎች ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሱት በጎችና በእነዚህ መሃል የማየው ተመሳሳይነት፤ ሁለቱም የእረኛቸውን የኢየሱስን ድምጽ ይሰማሉ፡፡ አማኞች ሁሉ አንድ እረኛ ብቻ ያላቸው ሲሆን፤ ኢየሱስ ደግሞ ያለው አንድ መንጋ ብቻ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡
8. ኢየሱስ ከተናገረው ውስጥ አይሁድን የከፋፈለው ሃሳብ እግዚአብሄር አባቱ እንደሆነ የተናገረው በቁ18 ላይ የሚገኘው ሃሳብ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ኢየሱስ ጋኔን ያደረበት እብድ እንደሆነና ሰዎች ሊሰሙት እንደማይገባ ሲናገሩ፤ ሌሎቹ ደግሞ የኢየሱስ ንግግር ጋኔን ያደረበት አይነት ሰው ንግግር እንዳልሆነና ጋኔና የአይነ ስውርን አይን መክፈት አይችልም በማለት ለእርሱ ሲቆሙ ይታያል፡፡
9. ኢየሱስ በዚህ ቁጥር ላይ ስላሚሟቱ የሚናገረው ሞቱ በፈቃደኛነት እንጂ በማንም አስገዳጅነት ወይም ራሱን ለማዳን ሃይል አጥቶ እንዳልሆነ ይናገራል፡፡ ኢየሱስ ነፍሱን ለመስጠት ስልጣን ሲኖረው መልሶ ለማንሳትም ጭምር ስልጣን እንዳለው ይናገራል፡፡

# ጥናት ሃያ ስምንት ዮሐንስ 10፡22-42 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው አይሁድ ኢየሱስን ማንነት አስመልክቶ ልባቸው እንደተንጠለጠለ መሆኑን እንረዳለን፡፡ የነዚህ ሰዎች ጥያቄ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን በግልጽ እንዲነግራቸው ነው፡፡
2. እርሱ እንደነገራቸው እነርሱ ግን እንደማያምኑ፤ በተጨማሪም ደግሞ የሚያደርጋቸው ተአምራቶች ስለእርሱ እንደሚናገሩ ነው የነገራቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በእርሱ የማያምኑበት ምክንያት የእርሱ በጎች ስላልሆኑ እንደሆነ ነው የነገራቸው፡፡ የእርሱ በጎች ድምጹን ይሰማሉ፣ እርሱም ያውቃቸዋል፣ እነርሱም ይከተሉታል፡፡
3. ኢየሱስን ሊወግሩ የተነሱበት ሃሳብ በሌሎችም ስፍራዎች እንደታየው ቁ30 ላይ አብን አባቴ በማለት መናገሩ ነው፡፡ የኢየሱስ ጥያቄ ከታላላቅ ተአምራት ስለየትኛው ትወግሩኛላችሁ? የሚል ነበረ፡፡ ለእነዚህ ሰዎች ስድብ አድርገው የቆጠሩት በቁ33 ላይ እንደምናነበው ኢየሱስን እንደተራ ሰው ማየታቸውና በቁ30 ላይ ደግሞ ኢኔና አብ አንድ ነን በማለት ራሱን ከእግዚአብሄር ጋራ አንድ ማድረጉ ለእነርሱ ስድብ ነው፡፡
4. መጽሐፍ ቅዱስ የማይሻርና ሊሻር የማይችል መጽሐፍ እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡ ስለ ኢየሱስ ማንነት ደግሞ የሚነግረን፤ አብ ለራሱ ለይቶ የቀደሰውና ወደ አለምም የላከው እንደሆነ እንረዳለን፡፡ እኔ የተረዳሁት ትክክለኛውን የኢየሱስ ማንነት እንኳን መረዳት ቢቸግራቸው በመዝ 82፡6 ላይ ሰዎች የሆኑት ዳኞች አማልክት ከተባሉ የእኔ የእግዚአብሄር ልጅ መባል ወይም እንደ አማልክት መቆጠር ለምን ይህንን ያህል አስቆጣችሁ ማለቱ ይመስለኛል፡፡
5. ተቃዋሚዎቹ እርሱ ራሱን የእግዚአብሄር ልጅ አድርጎ እንዳያቀርብ በተለያዩ ጊዜያት ተነግሮት ሳለ በዚህ ክፍልም ይህንኑ ደግሞ ሲናገር ነው የምንመለከተው፡፡ እያስተማረ ያለው ነገር እውነት ስለሆነና ሰሚዎቹ ስለተቃወሙ ብቻ እውነትን መቀየጥ ወይም አለመናገር ትክክል አለመሆኑን ስለሚያውቅ ነው፡፡ ሰዎቹም ሃሳባቸውን እንዳልቀየሩ የምናውቀው እንደገና ሊይዙት እንደሞከሩ በቁ39 ላይ ይታያል፡፡
6. ዮሐንስ በህይወቱ አንድም ተአምራዊ ምልክት እንዳላደረገ የሰፈረልን ሲሆን ከእርሱ በኋላ ስለሚመጣው መሲህ የተናገረው ነገር ግን አንድም ውሸት የማይገኝበት እውነት እንደሆነ እናነባለን፡፡
7. የዘላለም ህይወት ይሰጣቸዋል፣ ከቶ አይጠፉም፣ ከእጁ ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም፣ ከአብ የተሰጡት ናቸው፣ ከአባቱ እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም፡፡ የተያዙት በኢየሱስ እጅና በአብ እጅ ነው፡፡

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ ዮሐንስ 11፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል የምናያቸው ተዋናኞች፡ አልአዛር፣ ማርታ፣ ማርያም፣ ስሙ ብቻ የተነሳው ጌታ ናቸው፡፡ ማርያምን ያስተዋወቀን በጌታ ላይ ሽቱ አፍስሳ እግሩን በጠጉርዋ ያበሰችው እንደሆነች ይነግረናል፡፡ ይህችን ሴት በዚህ መልኩ ያስተዋወቀን ምክንያት እንደሚገባኝ ይህንን ቤተሰብ ኢየሱስ የሚወዳቸው ብቻ ሳይሆን እነርሱም በተለይም ማርያም ለእርሱ ያላትን ፍቅር ለመግለጽ ይመስለኛል፡፡
2. መልዕክቱ ‹‹ጌታ ሆይ የምትወደው ሰው ታሟል›› የሚል ነበረ፡፡ የኢየሱስ ምላሽም ህመሙ ለሞት የመጣ ሳይሆን የእግዚአብሄር ልጅ ይከብር ዘንድ ነው የሚል ነበረ፡፡ በኢየሱስ ምላሽ ውስጥ ከላይ ‹‹የእግዚአብሄር ልጅ ይከብር ዘንድ›› ብሎ ከታች ደግሞ ‹‹ለእግዚአብሄር ክብር ነው›› የሚለው የእግዚአብሄር ልጅ እግዚአብሄር እንደሆነ ይጠቁመናል፡፡
3. በ10፡31 ላይ እንደምንመለከተው ኢየሱስን ሊወግሩት እንደሞከሩ እንዳመለጠ ስለሚታወቅ ደቀ መዛሙርቱ ይህንን ምክንያት ነው ወደ ይሁዳ እንዳይሄድ የተጠቀሙበት፡፡ ኢየሱስ በብርሃን መመላለስን ሲናገር በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል አንዱ ሰዓቱ አስራ ሁለት ሰአት ስለሆነ ቀን ነውና መሄድ ይቻላል የሚል ሲሆን፤ ሌላው ግን በመንፈሳዊ አነጋገር በብርሃን ወይም በእግዚአብሄር ፈቃድ ውስጥ ሲመላለሱ የሚያስፈራ ነገር የለም የሚያስፈራው በጨለማ መኖር እንደሆነ ይናገራል፡፡
4. አልአዛር እንደተኛና እርሱም ከእንቅልፉ እንደሚያስነሳው አድርጎ ነው ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው፡፡ ኢየሱስ የሚናገረው በመንፈሳዊ አነጋገር ሲሆን፤ ደቀመዛሙርቱ ደግሞ ነገሮችን የሚያዩት በሥጋዊ መንገድ ነው፡፡
5. የደቀ መዛሙርቱ አስተሳሰብ ስሜት የማይሰጠው ከእንቅልፍ መቀስቀስ ከሆነ ሁለቱ እህቶቹና ጎረቤቱ ሊያደርግ የሚችለው ነገር መሆኑን አለማሰባቸው ነው፡፡ እኔ የሚመስለኝ ከሞት ማስነሳት የሚለው ነገር በአእምሯቸው የማይቻል እንደሆነ ስለገመቱ፤ ተአምሩን ከማሰብ መቀስቀሱ ቀሏቸው ሳይሆን አይቀርም እላለሁ፡፡
6. አንደኛው ምክንያት ሆኖ የምናነበው ደቀመዛሙርቱ እምነት ይሆንላቸው ዘንድ ነው፡፡ ቶማስ እውነቱ የአልአዛር እውነትም እንደሞተ ሲነገረው፤ ምንም እንኳን ኢየሱስ ለመገደል የሚፈለግ ቢሆንም አልአዛር ከሞት የሚነሳ ከሆነ ቢሞትም በህይወቱ ቆርጦ ለመሄድ እንደወሰነ እናነባለን፡፡
7. ኢየሱስ የእነማርያምን ቤተሰብ በ አጠቃላይ ይወድ እንደነበረ ይነግረናል፡፡ አልአዛር መታመሙን ሲሰማ ያደረገው ነገር ከነበረበት ስፍራ ሳይንቀሳቀስ ሁለት ቀናት እንደቆየ እንመለከታለን፡፡ ይህንን ያደረገበት ምክንያት እንደሚመስለኝ ከሆነ አልዓዛርን ምንም እንኳን ቢወደው እንዲሞትና እንዲቀበር ከዚያም ተአምራቱን ለማድረግ እንደሆነ ከአጠቃላይ ምዕራፉ መረዳት እንችላለን፡፡
8. እያንዳንዱ የራሱን መልስ ይስጥበት፡፡

## ጥናት ሰላሳ ዮሐንስ 11፡17-37 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል ውስጥ የማያቸው፡ ኢየሱስ፣ ደቀመዛሙርቱ፣ አልአዛር፣ ብዙ አይሁድ፣ ማርያም፣ ማርታ፡፡ ኢየሱስ በቢታንያ ሲደርስ አልአዛር ከሞተና ከተቀበረ አራት ቀን ሆኖት ነበረ፡፡
2. የኢየሱስን መምጣት አስቀድማ የሰማችው በቁ20 ላይ እንደምናነበው ማርታ ነች፡፡ እነዚህ እህትማማቾች ለኢየሱስ የተለየ አቀባበል ማለትም ሰዎቹን ትተው ወጥተው መቀበል ያስፈለጋቸው፤ ከእርሱ ጋራ የነበራቸው ግንኙነት፣ ለእርሱ ያላቸው ፍቅር፣ አክብሮትና ከሁሉ በላይ ደግሞ ለወንድማቸው መፍትሄ ሊያመጣ የሚችል ብለው የሚጠብቁት እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡
3. የመጀመሪያው እርሱ ቀደም ብሎ ቢገኝ ወንድማቸው እንደማይሞትና ሌላው ደግሞ እግዚአብሄር የሚለምነውን ሁሉ እንደሚሰጠው ነው፡፡ ኢየሱስን ወሰናዋለች የሚያሰኘው ከመሞቱ በፊት ቢደርስ ብቻ ከህመሙ ሊፈውሰው እንደሚችል፤ ነገር ግን ከሞተና ከሸተተ በኋላ እንዳለቀለት አድርጋ ነው ያቀረበችው፡፡
4. ማርያም የተረዳችው ወደፊት ስለሚሆነው ትንሳኤ የምታስብ ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን የሚናገረው የዛሬውን ትንሳኤ ነበረ፡፡ የወደፊቱን እንደሚያምኑ አድርጎ መናገር ይቀላል ብዬ አስባለሁ፣ ምክንያቱም የወደፊቱ የሁሉም ስለሆነ የህብረትና የጋርዮሽ እምነት አድርጎ ማስኬድ የሚቻል ሲሆን፤ ይህ የዛሬው ግን ወሳኝነት ያለው በግል ሰዎች ሁሉ የሚያዩትና የሚፈተን እምነት ስለሆነ ይሆናል ብሎ በድፍረት መናገር አስቸጋሪ የሚሆን ይመስለኛል፡፡
5. ኢየሱስ የሚናገረው ስለስጋዊ ሞት እንዳልሆነ ዕብ 9፡27 ስናነብ እንረዳለን፤ እየተናገረ ያለው ስለ መንፈሳዊ ሞት ነው፡፡ ትንሳኤና ህይወት ማለት ከእርሱ ውጭ ያለ የተለየ ሌላ ነገር ሳይሆን፤ ትንሳኤም ሆነ ህይወት ኢየሱስ ራሱ እንደሆነ ነው የሚያስረዳት፡፡
6. እህቷን ማርያምን ጠርታ ኢየሱስ እንደመጣና ደግሞም እንደሚፈልጋት ነው የነገረቻት፡፡ ማርያምም የኢየሱስን መምጣት ስትሰማ ፈጥና እንደተነሳችና ወደ እርሱ እንደሄደች እናነባለን፡፡ ኢየሱስ በሃሰን የተጎዳችውን ማርያምን ለመፈለግ ካለችበት ድረስ መምጣቱ እኛም ሃዘንና መከራ ባገኘን ጊዜ ኢየሱስ ካለንበት ቦታ ድረስ መጥቶ ሊያጽናናን እንደሚችል እማራለሁ፡፡
7. የተናገሩት አንዱ አልአዛርን እንዴት ይወደው እንደነበረ ያስተዋሉ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የአይነስውሩን አይን የከፈተ አልአዛርንም እንዳይሞት ማድረግ ይችል ነበረ የሚሉ ናቸው፡፡ እህትማማቾቹ ኢየሱስ ቀደም ብሎ ቢመጣ ወንድማቸው አልአዛር እንደማይሞት የተናገሩ ሲሆን፤ በዚህ ክፍል ደግሞ አይሁድ ከሞት የማስነሳቱን ሃይል ሳይሆን እንዳይሞት የማድረግ ወይም የመፈወስ ችሎታ እንዳለው ከተመለከቷቸው ተአምራቶች አንጻር ይችላል ብለው ተቀብለውታል፡፡
8. አይሁድ ይህንን የተናገሩበት ምክንያት በቁ35 ላይ ኢየሱስ አዝኖ እንባውን ሲያፈስ በማየታቸው ነበረ፡፡ ኢየሱስ የሚወደው ጓደኛ ሲሞት ማዘኑና ሃዘኑን በለቅሶ መግለጹ እኛም ለወዳጆቻችን ለማልቀስ ነጻነትን ይሰጠናል፡፡

## ጥናት ሰላሳ አንድ ዮሐንስ 11፡38-57 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሰዎቹን ያዘዛቸው ድንጋዩን እንዲያነሱት ነው፡፡ ይህንን ያደረገበት ምክንያት እንደሚመስለኝ ሰዎቹ ራሳቸው ያደረጉት ድርጊት ስለሆነና በራሳቸው ሊደረግ የሚችል ነገር ስለሆነ ይመስለኛል፡፡ ማርያም የመለሰችለት አልዓዛር ከሞተ አራት ቀናት እንደሆነው፣ እንደሸተተና ባይንቀሳቀስ እንደሚሻል ነው፡፡
2. ቁ25-26 ላይ ኢየሱስ ራሱ ትንሳኤና ህይወት መሆኑን የነገራትን ሃሳብ ነው፡፡ ኢየሱስ በቁ25-26 ላይ እርሱ ትንሳኤና ህይወት መሆኑን የተናገረው ከሞት ለማስነሳትም ሆነ ህይወት ለመስጠት ጊዜና ሁኔታ እንደማያግደው፣ አራት ቀንም ይቅርና አራት ሺህ አመታት ቢሆነው ህይወት ሊሰጠው እንደሚችል ልታምን እንደሚገባት ሲያረጋግጥ ነው፡፡
3. አባቱን አመሰገነ፣ የተናገረውን ነገር ለምን እንደተናገረ መግለጫ ሰጠ፣ በታላቅ ድምጽ አልአዛር እንዲወጣ ተጣራ፡፡ ይህንን የተናገረበት ምክንያት ቀደም ባሉት ክፍሎች እግዚአብሄር አባቴ ነው የሚለው ሃሳብ ብዙ ችግር ውስጥ እንዳስገባው የታወቀ ሲሆን፤ አሁንም ተአምራቱን ሲያደርግ እግዚአብሄርን ‹‹አባት ሆይ›› በማለት ልጅነቱን በማረጋገጥ እግዚአብሄር እንደላከው ማረጋገጫ ነው፡፡
4. ተአምራቱ ያስከተለው ነገር ብዙዎች በእርሱ ሲያምኑ፤ አንዳንዶች ግን ወረውን ለፈሪሳውያን አደረሱ፡፡ እግዚአብሄር የተናገረውን ቃል በእምነት ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ እንጂ ተአምር ማየት ብቻውን የሰውን ህይወት ሊለውጥ ስለማይችል ነው፡፡ ከዚህ መማር የሚቻው
5. በዚህ ክፍል የፈሪሳውያኑ ችግር የነበረው ኢየሱስ ብዙ ተአምሮችን ማድረጉና ዝም ብለው ቢተውት ሰዎች ሁሉ በእርሱ እንደሚያምኑ እርግጠኛ መሆናቸው ነው፡፡ በመፍትሄነት የቀረበው ሃሳብ ቀያፋ የሰጠው ሲሆን ይህም ኢየሱስ እንዲገደል የሚል ነው፡፡
6. ምክንያቱም አንዱ የእግዚአብሄር በግ ለህዝብ ሁሉ ሃጥያት ሊሞት እንደመጣ ለዚህም አላማ እግዚአብሄር እንደላከው የታወቀ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ አነጋገር ቀያፋ ሲናገር ነገሩ ገብቶትና ተረድቶ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ውስጥ እውነቱን በዚያ ለተገኙት ሰዎች ሲናገር እንደሆነ ለማሳየት ነው፡፡ ቁ52 ላይ የሰፈረው ሃሳብ ይህንን ይጠቁመናል፡፡
7. ፈሪሳውያን ኢየሱስን አጥብቀው እንደሚጠሉትና በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ህይወቱን ሊያጠፉት የተዘጋጁ እንደሆኑ በግልጽ እንመለከታለን፡፡ እነዚህ የህግ አስተማሪዎች በዚህ ባልሆነ ተግባር ውስጥ የተሰማሩት የራሳቸውን ክብር ስለሚፈልጉ፣ የእግዚአብሄርን ነገር ለመስማትና ለመቀበል ልባቸውን ስላላዘጋጁ፣ ከእነርሱ የበለጠ ተቀባይነት ማግኘቱና በትምህርቱ ሰዎች ሁሉ ስለሚሳቡ፣ ተአምራቱም ብዙዎችን ስለማረከ በቅናት መንፈስ መያዛቸው ሁሉ አስተዋጽዖ እንዳደረገ አልጠራጠርም፡፡
8. በዚህ ቁጥር ላይ ያዘዛቸው ‹‹መግነዙን ፍቱለትና ይሄድ›› በማለት ነበረ፡፡ ከዚየሱስ አነጋገር እንደምንረዳው አልዓዛር ምንም እንኳን ህይወትን ይዝራበት እንጂ ለመንቀሳቀስና እንደፈለገው ወዲያና ወዲህ ለማለት እንዳይችል የታሰረበት ነገር ስላለ ኢየሱስ በዚያ ዓይነት መቆየቱ ፈቃዱ ስላልነበረ ነው እንዲፈታ የፈለገው፡፡

# ጥናት ሰላሳ ሁለት ዮሐንስ 12፡1-19 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር ውስጥ የሚታዩት፡ ኢየሱስ፣ ማርታ፣ አልዓዛር፣ ማርያም፣ በማዕድ የተቀመጡ ሰዎች፡፡ አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ታሪኩን በአጭሩ እንዲናገሩ ዕድል ይሰጥ፡፡
2. ይህ የማርያም ድርጊት ያስከተለው ነገር ተቃውሞ ነበረ፡፡ ጥያቄውን በዋነኛነት ያቀረበው ሰው በኋላ ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደነበረ እናያለን፡፡ ዮሐንስ ለአንባቢያኑ ይሁዳ ይህንን የተናገረው ለድሆች ተቆርቁሮ ሳይሆን፤ ሌባ ስለነበረ ገንዘቡን ለራሱ ለመጠቀም ሲል እንደነበረ ይነግረናል፡፡
3. በአየቃላይ አነጋገር ኢየሱስ ሊል የፈለገው ነገር ሴትየዋን ተዋት፣ ለድሃ ከሆነ ያሰባችሁት ድሆች መቼም ቢሆን መኖራቸው አይቀርምና ልታደርጉላቸው ትችላላችሁ፡፡ ኢየሱስ ሂሳቡ ሳይገባው ቀርቶት ሳይሆን ዋናው ነገር ብዙ በጎ አድራጎት ማድረግ ሳይሆን የልብ ጉዳይ ነው ለማለት ነው የፈለገው፡፡
4. ኢየሱስንና አልዓዛርን ለማየት ነበረ፡፡ የብዙ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መምጣት ያስከተለው ነገር የካህናት አለቆችን እንዳናደደና በዚያም ምክንያት ኢየሱስን ብቻ ሳይሆን አልአዛርንም ጨምሮ ለመግደል ተማከሩ፡፡ አልአዛርን ለማየት የመጡት ሰዎች በኢየሱስ ያምኑበት ነበረ፡፡
5. ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዎች በአጭሩ እንዲናገሩ ዕድል ይሰጥ፡፡ ኢየሱስ የእነዚህን ሰዎች ድርጊት እንደተቀበለው የሚያስረዳን ክፍል በቁ14 ላይ የምናየው ሃሳብ ነው፡፡
6. ስለኢየሱስ ስራ በዚህ ክፍል ይመሰክሩ የነበሩት የአልዓዛርን ከሙታን መነሳት በዓይናቸው ያዩት ሰዎች እንደነበሩ ይታያል፡፡ ‹‹ሆሳዕና›› በማለት ለብዙዎች የደስታ ጊዜ ሲሆን፤ የሃዘን ጊዜ የሆነው በቁ19 ላይ እንደምናየው ለፈሪሳውያኑ ነው፡፡ ‹‹ዓለሙ ሁሉ ግልብጥ ብሎ ተከትሎታል›› የሚለው አነጋገር ተከታዮቹ እጅግ ብዙ ቁጥር እንደሚኖራቸው ይጠቁማል፡፡
7. በዚህ ክፍል ውስጥ አልዓዛር ለግብዣው ከመጡት ሰዎች ጋራ እንደ አንደኛቸው ተቀምጦ የሚቀርብለትን ምግብ ለመብላት በመጠባበቅ ላይ እንዳለ ነው የምንመለከተው፡፡

# <u>ጥናት ሰላሳ ሶስት ዮሐንስ 12፡20-50 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ፊሊጶስ በእነዚህ ሰዎች የተጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስን እንዲያሳያቸው ነው፡፡ ፈሪሳውያኑ ማየት የሚፈልጉት ኢየሱስ የሚሰራውን ተአምራት ሲሆን፤ እነዚህ ግሪኮች ግን ማየት የፈለጉት ራሱን ኢየሱስን ነበረ፡፡ ለጥያቄያቸው የወሰደው እርምጃ በመጀመሪያ ለእንድርያስ እንደነገረውና ከዚያም ሁለቱ ተያይዘው ሄደው ለኢየሱስ እንደነገሩት እንመለከታለን፡፡
2. ኢየሱስ በቁ23 ላይ እንደክብር አድርጎ የሚናገረው ነገር ሞቱን ነው፡፡ በመስቀል ላይ የሚሞት የተረገመ መሆኑ እውነት ሲሆን፤ ነገር ግን ኢየሱስ ለራሱ ሃጥያት ሳይሆን ለሌሎች ሃጥያት በመሞቱ በአባቱ አመለካከት ክብር ነው፡፡ ኢየሱስ ህይወቱን የተመለከተው እንደስንዴ ቅንጣት ሲሆን እርሱ ካልሞተ ሌሎች ህይወትን ሊያገኙ እንደማይችሉ ስለሚያውቅ ነው፡፡
3. ኢየሱስ በዚህ ክፍል ወደ መስቀል የመሄዱ ሰዓት እየደረሰ ስለሆነ እንደ ሰው የነበረውን ፍርሃትና ጭንቀት ሲናገር እናየዋን፡፡ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ብሎ ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ የሚስበው በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ በመሞት ሰዎችን ሁሉ ወደ እርሱ ማለትም ወደዘለዓለም ህይወት ማምጣቱ ነው፡፡
4. ሁለቱ ጥያቄዎች፡ የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ማለት አለበት እንዴት ትላለህ? (ከህግ መጽሃፍ ጋራ ይቃረናል) እና የሰው ልጅ ማነው? የሚሉት ናቸው፡፡ የኢየሱስን መልስ ጠለቅ ብለን ስንመለከት ሊላቸው የፈለገው ዋነኛ ሃሳብ፤ እኔ የአለም ብርሃን ስለሆንኩ በእኔ እመኑ፣ በብርሃንም ተመላለሱ የሚል ነው፡፡
5. በቁ37 ላይ ለሚታዩት ተአምራቶች ሁሉ እያዩ ነገር ግን በኢየሱስ ለማመን አሻፈረኝ በማለት ልባቸውን ላደነደኑት ሰዎች ነው፡፡ በቁ42-43 ደግሞ በኢየሱስ ያመኑና ነገር ግን ፈሪሳውያንን ፈርተው ማመናቸውን መግለጥ ያልፈለጉ ሰዎች ይታያሉ፡፡ ራሳቸውን ያልገለጡበት ምክንያት ፈሪሳውያን ከምኩራባቸው እንዳያስወጧቸው ነው፡፡ ዮሐንስ ይህንን የሚገልጠው ‹‹በእግዚአብሄር ከመመስገን ይልቅ በሰው መመስገንን ስለወደዱ ነው›› ይላል፡፡
6. በኢየሱስ ያመነ በአብም እንዳመነ፤ ኢየሱስን ያየ አብንም እንዳየ በማለት አብን ከወልድ፣ ወልድን ከአብ መለየት እንደማይቻል ነው፡፡
7. የኢየሱስን ቃል በሚያቃልሉት ላይ በመጨረሻው ቀን የሚፈርደው ኢየሱስ የተናገረው ቃል ሲሆን፤ ለዚህም ምክንያት አድርጎ ያቀረበው ነገር፣ ኢየሱስ ሲናገር ከራሱ ፈጥሮ እንደማይናገርና የላከው አብ መን እንደሚናገርና እንዴት እንደሚናገር እንዳዘዘው፣ እርሱም በዚያ መሰረት ብቻ ስለሚናገር ቃሉ ይፈርድባቸዋል፡፡
8. እነዚህ ሰዎች ትኩረታቸውን በኢየሱስ ላይ ያደረጉት፤ ምናልባትም የኢየሱስ ትምህርትና ያደረጋቸው ተአምራቶች፣ ስለራሱም ማንነት የተናገራቸው ንግግሮች እውነትም አምልኮ ሊሰጠው የሚገባው መሆኑን ተገንዝበው ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡

## ጥናት ሰላሳ አራት ዮሐንስ 13፡1-38 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሙሉ ፍቅሩን የገለጠበት መንገድ እንደ ባርያ እግራቸውን በማጠብ ነበረ፡፡ ኢየሱስ እንዳወቀ የሚናገራቸው፡ ወደ አብ የሚሄድበት ጊዜ እንደደረሰ፣ አብ ሁሉን በስልጣኑ ስር እንዳደረገለት፣ ከእግዚአብሄር እንደተላከ እና ወደ እግዚአብሄርም እንደሚመለስ ነበረ፡፡ እነዚህን አወቀ ካለን በኋላ የደቀመዛሙርቱን እግር እንዳጠበ ይነግረናል፤ እርሱ ታላቅ መሆኑን አውቆ እግር ካጠበ፣ እኛ ከርሱ የእርሱ አይነት ክብር ስለሌለን ዝቅ ለማለት መማር ይገባናል፡፡
2. ካላጠብኩህ ከእኔ ጋራ እድል የለህም ሲል፤ ሃጥያትህን እኔ ካላጠብኩህ ከእኔ ጋራ ህብረት ሊኖርህ አይችልም ማለቱ ሲሆን፣ ጴጥሮስ ግን የኢየሱስን ንግግር ቃል በቃል ወስዶ በውሃ እግሩን፣ እጁንና መላ ሰውነቱን ከመታጠብ ጋራ ነበረ የተረዳው፡፡
3. ኢየሱስ እንዲያደርጉ ያዘዛቸው ነገር እርስ በእርሳቸው እግራቸውን እንዲተጣጠቡ ነው፡፡ የሰጣቸውም ምክንያት እሱ ጌታቸውና መምህራቸው ሆኖ ይህንን ካደረገና ምሳሌን ከተወላቸው፤ እነርሱም ከአስተማሪያቸው ስለማይበልጡ እንዲሁ ሊያድርጉ ይገባቸዋል፡፡ በረከትን የሚያይዘው ከማወቅ ጋራ ብቻ ሳይሆን፣ አውቆ ከመታዘዝ ወይም ከመፈጸም ጋራ ነው፡፡
4. ይህ አነጋገር ስለኢየሱስ ማንነት የሚነግረን፤ ገና ያልሆነውን ነገር አስቀድሞ ማወቅ መቻሉ አምላክነቱን ያረጋግጥልናል፡፡ ይሁዳን በክፉ አይን እንደማያየው የምናውቀው አንደኛ፤ እያወቀው እርሱን ለገንዘብ ያዥነት መሾሙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ ክፍል እንደምናነበው ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ አስቀድሞ ይሁዳን በክፉ አይን እያየው ቆይቶ ቢሆን ኖሮ ይህንን ንግግር ሲናገር በቀጥታ ሁሉም ወደሱ ያዩ ነበረ፤ ነገር ግን ቁ22 ግራ ተጋብተው እርስ በእርሳቸው ተያዩ›› ነው የሚለን፡፡
5. በሁለቱ ቁጥሮች ውስጥ በብዛት የተጠቀሰው አንድ ቃል መክበር የሚለውቃል ነው (5 ጊዜ)፡፡ ኢየሱስ አብን በሞቱ ያከበረው ዮሐ 17፡4-5 እንደሚነግረን ገና በመስቀል ላይ ባይወጣም እርሱ ግን ራሱን ለመስጠት የቆረጠ ስለሆነ እንደሞተ በመቁጠር አብ የሰጠውን ሥራ ማለትም ለሰው ልጆች ደህንነት መሞትን እንደፈጸመና እንዳከበረው ይነግረናል፡፡ ፊሊ. 2፡8-9 ማንበብ ይረዳል፡፡
6. ኢየሱስ ሊያስተምራቸው የፈለገው ነገር እርስ በእርስ እንዲዋደዱ ነው፡፡ ኢየሱስን መውደዳችንን የምናሳይበት ዋነኛ መንገድ እርስ በእርሳችን በመዋደድ ነው፡፡
7. ጴጥሮስ ኢየሱስን መውደዱን ማሳየት የፈለገበት መንገድ እርሱን በመከላከልና ከእርሱ ባለመለየት፣ ለእርሱ በመቆም ፍቅሩን መግለጥ የሞከረ ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን አጠገቡ የሚቀሩትን ወንድሞቹን በመውደድ ኢየሱስን መውደዱ እንደሆነ ነው ያስተማረው፡፡ ትኩረት እንዳልሰጠ የሚመስለው ቁ36 ላይ የሚጠይቀው ጥያቄ ከላይ በቁ33-34 ላይ ለተነገረው ነገር የበለጠ ትኩረት የሰጠ ይመስላል፡፡
8. ኢየሱስ ጌታው እንጂ ባሪያው ስላልሆነ በእርሱ እግሩን መታጠብ ነውር እንደሆነ ቆጥሮ ነው፡፡ ለዚህም የኢየሱስ ምላሽ ኢየሱስ ነገሩ አሁን እንደማይገባው፣ ቆይቶ ማለትም በኋላ ግን እንደሚያስተውል ነገረው፡፡

## ጥናት ሰላሳ አምስት ዮሐንስ 14፡1-31(ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ደቀመዛሙርቱን ያጽናናቸው ተመልሶ መጥቶ ወደእርሱ እንደሚወስዳቸው በመንገር ነው፡፡ ኢየሱስ ሥፍራ አዘጋጅቶ ተመልሶ በመምጣት እንደሚወስዳቸውና በዚያ ከእርሱ ጋራ እንደሚኖሩ ሲናገር፤ ጳውሎስም በተመሳሳይ መንገድ ጌታ ሲመጣ ሁላችንም ከእርሱ ጋራ በደመና በመነጠቅ ወደእርሱ መሄዳችንን ለእርስ በእርሳቸው መጽናኛ እንዲያደርጉት ለተሰሎንቄ አማኞች ይነግራቸዋል፡፡
2. ይህ ብዙዎች የሚቆጡበት ንግግር በቁ6 ላይ ‹‹…በእኔ በኩል ካሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡›› የሚለው አነጋገር ነው፡፡ በዘመኑ የእውነት መለኪያ የሆነ አንድ እውነት አለ ተብሎ ስለማይታመን እያንዳንዱ ሰው የያዘው እውነት ለራሱ እውነት ነው፤ ስለዚህም ማንም የእኔ እውነት ከአንተ እውነት ይበልጣል ማለት ስለማይቻል ነው የኢየሱስ አነጋገር ለብዙዎች የሚከብደው፡፡
3. ኢየሱስን ስናውቅ አብንም ማወቃችን ነው፣ ደግሞም ኢየሱስን ስናይ አብን አይተናል ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ አብን የገለጠው ሥጋን ለብሶ በመሃላችን በመገኘትና በመመላለስ ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ አብን እንደገለጸው፤ እንዲሁም ዕብ 1፡3 የክብሩ መንጸባረቅ ሆኖ ትክክለኛ የአብን ማንነት እንደገለጸልን ይነግረናል፡፡
4. ለደቀመዛሙርቱ በዚህ ክፍል የገባላቸው ተስፋ አብን ለምኖ መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጣቸው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለዘለዓለም የሚኖር ነው፣ አጽናኝ ነው፣ የእውነት መንፈስ ነው፣ ዓለም አያየውም፣ ዓለም አያውቀውም፣ እኛ እናውቀዋለን፣ በውስጣችን ይኖራል፣ አብሮን ይኖራል፡፡
5. ይህ አዲስ ተስፋ ነው አልልም፤ ምክንያቱም በቁ3 ላይ ስንመለከት ይህንኑ አስረግጦ ሲነግራቸው እናያለን፡፡ ወላጅ የሌላቸው ልጆች በአብዛኛው ተስፋ የቆረጡ፣ የሚያስፈልጋቸውን የማያገኙ፣ ፍቅርን የማያገኙ… እና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ በተለይ ቁ20ን ስናነብ ኢየሱስ በአባቱ፣ እኛ በኢየሱስ፣ ኢየሱስ ደግሞ በእኛ ውስጥ እንደሚኖር ስናነብ ምን ያህል ሥፍራ እንደሰጠን መረዳት ይቻላል፡፡
6. ኢየሱስን መውደድ የሚገለጠው ትዕዛዙን በመጠበቅ (ቁ21) ወይም ቃሉን በመጠበቅ (ቁ23) ነው፡፡ አባቴ ይወደዋል(21)፣ እኔም እወደዋለሁ(21)፣ ራሴን እገልጥለታለሁ(21)፣ ወደ እርሱ እንመጣለን(23)፣ ከእርሱ ጋራ እንኖራለን(23)፡፡
7. መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያስተምረናል፣ ጌታ የነገረንን ሁሉ ያሳስበናል፡፡ በሁለቱ ሰላሞች መሃል ያለው ዋነኛ ልዩነት እኔ እንደሚገባኝ አለም የሚሰጠው ሰላም ጊዜያዊ ሲሆን፤ ኢየሱስ የሚሰጠው ግን ቋሚና ዘላቂነት ያለው ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የዓለም ሰላም በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ የኢየሱስ ሰላም ግን በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ ነው፡፡
8. በአባቱ ቤት ብዙ መኖሪያ እንዳለ ተናግሯል(ቁ2)፣ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ(16)፣ ተመልሶ እንደሚመጣ(3፣ 18፣ 28)፡፡ ተደጋግሞ የተነገረው የማጽናኛ ሃሳብ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ ነው፡፡

# ጥናት ሰላሳ ስድስት ዮሐንስ 15፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ ራሱን እንደ እውነተኛው የወይን ተክል ሲያስተዋውቅ፤ አባቱን ደግሞ እንደ አትክልተኛ አድርጎ ያቀርባል፡፡ በነዚህ ቁጥሮች አነጋገር ሁለት አይነት ቅርንጫፎች ይታያሉ፤ እነርሱም የማያፈሩና የሚያፈሩ ተብለው ተለይተዋል፡፡ መግረዝ ማለት ለማስተካከልና ለበለጠ ፍሬ ለማብቃት የሚደረግ ሲሆን፤ መቁረጥ ግን የተተከለበትን መሬት ከማራቆት በስተቀረ ለማፍራት ምንም ዓይነት ተስፋ እንደሌለው በመረዳት ከስፍራው ለማስወገድ የሚደረግ ድርጊት ነው፡፡
2. እነዚህ ቁጥሮች ያተኮሩበት ሃሳብ አማኝ በክርስቶስ መኖር እንዳለበት ነው፡፡ ለክርስትያን ፍሬ ለማፍራትም ሆነ ላለማፍራት ወሳኙ ነገር በኢየሱስ ውስጥ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ነው፡፡ ይህንን ሲል ልክ ቅርንጫፍ ከግንዱ ጋራ ተጣብቆ ሳለ ማናቸውም ግንዱ ያለው ነገር ሁሉ ያለችግር እንደሚተላለፍና ለእድገት እንደሚሆነው፤ እኛም በክርስቶስ ውስጥ ስንኖር የእርሱ ህይወት በእኛ ውስጥ አስፈላጊውን ህይወት እንደሚፈጥር ለማስረዳት ነው፡፡
3. ደቀመዝሙርነታችንን የምንገልጸው ብዙ ፍሬን በማፍራት ነው (ቁ8)፣ እግዚአብሄርን የምናከብርበት መንገድ ሆኖ በዚህ ክፍል የተነገረው ብዙ ፍሬን በማፍራት ነው፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ፍሬ እያለ የሚናገረው በገላቲያ ምዕራፍ አምስት ውስጥ የመንፈስ ፍሬ በማለት የሚናገራቸውን ነው፡፡
4. ወዳጆቹ የምንሆነው የሚያዘንን ብንፈጽም ነው፡፡ በዚህ ክፍል ያዘዘንና ምሳሌነትም የተወልን ነገር እርስ በእርስ መዋደድን ወይም ስለ ወዳጅ ህይወትን አሳልፎ መስጠትን ነው፡፡ አገልጋይ እዚሁ ከምናነበው ጌታው የሚሰራውን እንደማያውቅ ሲነገረን፤ ወዳጅ ግን በልብ ያለውን ሁሉ የሚያጫውቱት የቅርብ ሰው መሆኑን እንመለከታለን፡፡ እኔ ወዳጅ ነኝ ብዮ ነው የማምነው፤ ምክንያቱም በእግዚአብሄር ልብ ያለውን የዘላለም ሃሳቡን ኢየሱስ ስለነገረኝ ማለት ነው፡፡
5. ኢየሱስን አስቀድሞ ስለጠላ(18)፣ ከዓለም ስላይደለን(19)፣ አገልጋይ ከጌታው ስለማይበልጥ(20)፣ ኢየሱስን የላከውን ስለማያውቁ(21)፡፡ ለደቀመዛሙርቱ ማስተማር የፈለገው እውነት እኔ እንደምረዳው፤ አለም እንዲወዳችሁ አትጠብቁ ምክንያቱም እኔን ጌታችሁን ካልወደደ እናንተንም አይወድም የሚል ነው፡፡
6. የመጀመሪያው ኢየሱስ ራሱ ከአብ ዘንድ መጥቶ የደህንነትን መልዕክት ማምጣቱና፤ ሁለተኛው ደግሞ ሌላ ሰው አድርጎ የማያውቃቸውን ተአምራቶች በመሃላቸው ማድረጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚጠሉት ወልድን(23፣ 24)፣ አብን(23፣ 24)፣ የየሱስን ተከታዮች(18፣ 20)፡፡
7. የሚያበረታታን ትዕዛዙን እንድንጠብቅና በፍቅሩ እንድንኖር ነው፡፡ የመታዘዛችንና በፍቅሩ የመኖራችን ውጤቱ፤ እግዚአብሄር በእኛ መደሰቱና የእኛ ደግሞ ደስታ ሙሉ መሆን ነው፡፡

# ጥናት ሰላሳ ሰባት ዮሐንስ 16፡1-33

1. ይህ አነጋገር የወደፊቱን ገና ሳይሆን መናገር የሚችል እግዚአብሄር ብቻ ሳለሆነ እግዚአብሄርነቱን ያረጋግጣል፡፡ ኢየሱስ ስለተከታዮቹ እንደሚጠነቀቅ የሚያሳየን ‹‹ይህንን የነገርኋችሁ እንዳትሰናከሉ ነው፡፡›› የሚለው አነጋገሩ ነው፡፡
2. አለምን አስመልክቶ የሚያደርገው አንድ ነገር መውቀስ ነው፡፡ በቁ6 ላይ እንደምናነበው መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት የማጽናናትን ስራ ሲሰራ፤ ባላመነ ሰው ውስጥ ደግሞ የወቀሳን ስራ እንደሚሰራ ከቁ7 እናያለን፡፡
3. በዚህ ክፍል ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ስም፡ የእውነት መንፈስ የሚል ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አጽናኝ ነው፣ ወደ እውነት ሁሉ ይመራል፣ ወደፊት የሚሆነውን ይነግረናል፣ የኢየሱስ የሆነውን ነገር እንድናውቅ ያደርጋል፡፡ ‹‹ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡›› ሲል ኢየሱስ የተናገረውንና በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ የተጻፈውን ለመረዳት እንድንችል ያደርገናል ማለቱ ነው፡፡
4. ለደቀመዛሙርቱ ጥያቄ የሆነው ነገር በቁ16 ላይ የተናገረው አነጋገር ነው፡፡ ከዚህ አባባሉ እኔ የሚገባኝ ‹‹ከጥቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም›› ሲል በሞት መለየቱን የሚገልጽ ሲሆን፤ ‹‹ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ›› ማለቱ ከሞት ተነስቶ እንደሚያዩት ሲጠቁም ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ለዚህ መልስም የተመረኮዝኩት በቁ20-22 ላይ ኢየሱስ የተናገራቸውን ሃሳብ በመያዝ ነው፡፡
5. ደቀመዛሙርቱ የሚያለቅሱትና ዓለም ሃሴት የሚያደርገው ኢየሱስ ሲሞት ሲሆን፣ የደቀመዛሙርቱ ሃዘን ደግሞ ወደ ደስታ የሚለወጠው ኢየሱስ ከሞት ሲነሳ ነው፡፡ የደቀመዛሙርቱን ጥያቄ ለኢየሱስ ማንም ሳይነግረው ራሱ ነው ያወቀው፡፡
6. ኢየሱስ ከእነርሱ ጋራ ሳለ በአብዛኛው ለሚያስፈልጋቸው ነገር ኢየሱስ ነበረ የሚጸልይላቸው፣ አሁን ግን ኢየሱስ ሲሄድ ራሳቸው በኢየሱስ ስም ጸልየው ከአብ በቀጥታ መቀበል እንደሚችሉ ነው የሚያረጋግጥላቸው፡፡ አብ ደቀመዛሙርቱን የሚወድባቸው ሁለት ምክንያቶች በቁ27 ላይ እንደ ምናነበው ኢየሱስን ስለወደዱትና፣ ከእግዚአብሄር እንደመጣ ስላመኑ ነው፡፡
7. ደቀመዛሙርቱን ያስጠነቀቃቸው በዓለም ሳሉ መከራ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ነው፡፡ ለማበረታታት የተናገራቸው ነገር እርሱ አለምን እንዳሸነፈና እንዳይፈሩ መንገር ነው፡፡ በቁ33 ላይ የተናገረው፡ በእርሱ ሰላም እንዲኖራቸው፤ ማለትም በሚመጣባቸው መከራና በሚያልፉበት ነገር ሁሉ እርሱ አብሯቸው እንዳለ ደግሞም እርሱ ዓለምን ስላሸነፈ በእርሱ ተደላድለው እንዲኖሩ ነው፡፡
8. ያዘኑበት ምክንያት በቁ5 ላይ እንደምናነበው አብሯቸው የነበረው ኢየሱስ ሊሄድባቸው እንደሆነ ስለሰሙ ነው፡፡ እርሱ መሄዱ እንደሚሻል የተናገረበት ምክንያት አጽናኝ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ወደ እነርሱ ስለሚመጣና በእነርሱ ውስጥ እንደሚኖር ስላወቀ ነበረ፡፡

# ጥናት ሰላሳ ስምንት ዮሐንስ 17፡1-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ይህንን ከተናገረ በኋላ የሚለን በምዕ13 ላይ እግራቸውን አጥቦ፤ ከምዕራፍ 14 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 16 መጨረሻ ድረስ የመከራቸውንና ያስተማራቸውን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ኢየሱስ የተቀበለው ስልጣን ከአብ ለተቀበላቸው ሁሉ የዘላለም ህይወትን የመስጠት ስልጣን ነው፡፡ በኢየሱስ አነጋገር የዘላለም ህይወት ማለት እውነተኛ አምላክ የሆነውን አብንና፤ የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው፡፡
2. ከአባቱ የተቀበለው ሥራ ለሰው ልጆች ሃጥያት ሞቶ ደህንነትን መስጠት ሲሆን፤ ይህ ሥራው ገና ተፈጽሟል ብዬ አላምንም፤ ምክንያቱም ገና ኢየሱስ አልሞተምና ነው፡፡ ኢየሱስ ይህንን ያለው ለእኔ እንደሚገባኝ ከሆነ እርሱ የአብን ትዕዛዝና የተላከበትን ጉዳይ ለመፈጸም ከልቡ የቆረጠ በመሆኑ ልክ እንዳደረገው ያህል ስለሚቆጥረው ነው፡፡
3. ቃሉን ጠብቀዋል፣ ኢየሱስ የተቀበለው ሁሉ ከአብ እንደሆነ አውቀዋል፣ የሰጣቸውን ቃል ተቀብለዋል፣ ኢየሱስ ከአብ እንደወጣ አውቀዋል፣ አብ እንደላከው አምነዋል፡፡ ኢየሱስ እየጸለየ ያለው አብ ለኢየሱስ ለሰጠው ሰዎች ብቻ እንጂ ለአለም አይደለም፡፡
4. በዚህ ክፍል የኢየሱስ ጸሎት ያተኮረው በአማኞች አንድነት ላይ ነው፡፡ ለአብ ያለው ሁሉ የወልድ እና ለወልድ ያለው ሁሉ ደግሞ የአብ እንደሆነ እንጂ በግለኛነት ላይ ያተኮረ አንድነት እንዳልሆነ ያሳያል፡፡
5. እነዚህን ቁጥሮች ስንመለከት የእግዚአብሄር ቃል ከእግዚአብሄር የመነጨና የተቀበለው ሁሉ ወደሌላው ትውልድ ሊያስተላልፈው የሚገባ የተቀደሰ ነገር እንደሆነ ነው፡፡ ቃሉን የተቀበለ ሰው ከዓለም እንዳይደለና ዓለም እንደምትጠላው እናነባለን፡፡
6. ኢየሱስ የሚልካቸው ወደሚጠሉበት ወደ ዓለም ነው፡፡ ከተልዕኮው በፊት የጸለየላቸው በእውነቱ እንዲቀድሳቸው ሲሆን፤ ይህም መቀደስ የሚለው መለየት ማለት ሲሆን፤ ለተልዕኳቸው የሚኖረውም አስተዋጽዖ ራሳቸውን በዓለም ነገር ሳያንድፉ ለተለዩለት ጌታ ተሰጥተው በሙሉ ልብ እንዲሰሩለት ይሆናሉ፡፡
7. በቁ1-19 የሚጸልየው ለደቀመዛሙርቱና በዚያን ሰዓት ላመኑት ሲሆን፤ በሁለተኛው ክፍል ማለትም በቁ20-26 ደግሞ ገና ከደቀመዛሙርቱ ወንጌልን ሰምተው ለሚያምኑት ነው፡፡ ይህ ለአማኞች የተሰጠው ክብር አብ በወልድ ውስጥ እንዳለ፤ የወልድ በአማኝ ውስጥ የመሆን ምስጢር ሲሆን፤ አብና ወልድ አንድ እንደሆኑ፤ አማኞችም አንድ እንዲሆኑ ዋነኛው መሰረት እንደሆነ እናያለን፡፡
8. ይህንን የሚያስረዳን ክፍል ቁ26 ሲሆን ኢየሱስ በመጀመሪያ ደረጃ እንዲያውቁህ አድርጌአለሁ ሲል ቀጥሎ ደግሞ ወደፊትም ገና እንዲያውቁህ አደርጋለሁ የሚለው አነጋገሩ ነው፡፡

# ጥናት ሰላሳ ዘጠኝ ዮሐንስ 18፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ምክንያቱም ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ ከደቀመዛሙርቱ ጋራ በአትክልቱ ሥፍራ ስለሚገናኝ ነበረ፡፡ ለመያዝ የመጡት፡ ወታደሮች፣ የካህናት አለቆችና፤ ከፈሪሳውያን የተላኩ ሎሌዎች ሲሆኑ ይዘው የመጡትም፤ ችቦ፣ ፋኖስና የጦር መሳሪያ ነበረ፡፡
2. በቁ4-5 ላይ የምናያቸው ሰዎች ኢየሱስን የፈለጉት ህይወቱን ሊያጠፉ፣ ሊገድሉትና ሊያዋርዱት ሲሆን፤ በዮሐ 12፡20-21 ላይ የሚፈልጉት ግን ምናልባትም በዚያ የተገኙበት ምክንያት ለአምልኮ ስለሆነ፤ የኢየሱስን ዝና ሰምተው ሊያመልኩትና ሊሰግዱለት እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡
3. በቃሉ እንደዚህ የመጣል ችሎታ እንዳለው ስመለከት እውነትም ይህ ሰው ከሰዎች የተለየ ዓይነት ሰው እንደሆነና በማየት የመጣሁበትን ዓላማ እንደምጠይቅ አስባለሁ፡፡ እርሱ ራሱ ወደ መከራ ውስጥ እየገባ እያለ ለተከታዮቹ እንደሚያስብ የሚጠቁምን በቁ8 ላይ የምናነበው ‹‹እነዚህ ይሂዱ ተውአቸው›› የሚለው አነጋገሩ ነው፡፡
4. ቀያፋ በዚያን ዓመት ሊቀ ካህናት ሲሆን፤ አይሁድንም የመከረው ‹‹ለህዝቡ ሲባል አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል፡፡›› በማለት ነበረ፡፡
5. የቀያፋ ጥያቄ ያተኮረው በኢየሱስ ትምህርትና በደቀመዛሙርቱ ላይ ነበረ፡፡ ኢየሱስም የመለሰው፤ ትምህርቱን ያስተማረው በግልጽ እንደነበረና ምንም ዓይነት በስውር ያደረገው ነገር ስለሌለ ትምህርቱን የሰሙትን ሰዎች እንዲጠይቅን እንዲረዳ ነበረ፡፡
6. ኢየሱስ ለሊቀ ካህናቱ የመለሰው መልስ ያስከተለበት ነገር ጥፊ ነበረ፡፡ ጥፊ ለመታው ሰውም የመለሰው ምላሽ በቁ23 ላይ የተናገረው ቃል ነው፡፡ ከዚህ ከኢየሱስ አነጋገር ልንማር የምንችለው ዋነኛ ነገር ቢኖር፤ ምስክርነታችን ሃሰተኞችን በማጋለጥ ላይ እንጂ እውነትን በያዙና በእውነት በሚመላለሱ ሰዎች ላይ በሃሰት ልንመሰክር እንደማይገባን ያስተምረናል፡፡
7. እርሱ ብቻውን እንዲወሰድና ደቀመዛሙርቱን ግን እንዲተውአችውና እንዲሄዱ ነበረ ኢየሱስ የተናገረው፡፡ ጴጥሮስ ኢየሱስ በቁ8 ላይ እንደተናገረው አቅሙን አውቆ መሄዱን ትቶ በሉቃ 22፡33 ላይ የፎከረውን ሥራ ላይ ለማዋል ኢየሱስ ወደገባበት ለመግባት ሙከራ ማድረጉ ነው፡፡ ይህንን ማድረጉ ለክህደት፤ ማለትም ለሃጥያት እንዳጋለጠው እንመለከታለን፡፡

# ጥናት አርባ ዮሐንስ 18፡28-19፡16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነርሱ ለጲላጦስ የሰጡት ምክንያት ‹‹በማንም ላይ የሞት ፍርድ ለመፍረድ መብት የለንም›› በማለት ሲሆን፣ በቁ32 ላይ እንደምናነበው ግን ይህ የሆነበት ምክንያት የእግዚአብሄር ቃል ማለትም ኢየሱስ አስቀድሞ የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ እንደሆነ እንረዳለን፡፡
2. ጥያቄው ‹‹አንተ የአይሁድ ንጉስ ነህን?›› የሚል ሲሆን፤ የኢየሱስ መልስ ግን የራሱ ውሳኔና አመለካከት ላይ ሊያደርስ የሚያስችለው ቀጥተኛ ጥያቄ በመጠየቅ ነው የመለሰለት፡፡
3. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በጲላጦስና በኢየሱስ መሃል የተካሄደው ውይይት የኢየሱስን ንጉስ መሆን አስመልክቶ ነው፡፡ ጲላጦስ ከኢየሱስ ለመማር የጠየቀው ጥያቄ ‹‹እውነት ምንድነው?›› የሚል ነው፡፡
4. ይህንን ማለት የምንችለው ጲላጦስ መርምሮ በደል እንዳላገኘበት ሲነገራቸውና ኢየሱስንም በፋሲካ አንድ እስረኛ ማስፈታት እንደሚችሉ ሁሉ አሳስቧቸው አነርሱ ግን በከፋታቸው መቀጠልን ወሰኑ፡፡ አይሁድ ከወንበዴ ይልቅ ጻድቁ እንዲሞት ሲመርጡ ነው የምንመለከተው፡፡
5. ኢየሱስ የራሱ የሆነ ሃጥያት እንደሌለበትና ነገር ግን ለሰዎች ልጆች ሃጥያት ሲል እንደሞተ በ2ኛ ቆሮ 5፡21 የምናነብ ሲሆን፤ ከላይ በተዘረዘሩት ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ ጲላጦስ በዚህ በዚያም እያለ ስህተት ቢፈልግበት ሊያገኝበት እንዳልቻለ መናገሩ ይህንን እውነት ያረጋግጥልናል፡፡
6. ቁ7 እንደሚነግረን በአይሁድ አመለካከት ኢየሱስ ሊሞት የሚገባው ራሱን የእግዚአብሄር ልጅ ስላደረገ ነው፡፡ ከሮሜ 13፡1 ጋራ የሚስማማው እውነት በዮሐ 19፡11 ላይ ያለው ‹‹ከላይ ባይሰጥህ ኖሮ በእኔ ላይ ሥልጣን ባልኖረህ ነበር›› የሚለው ሃሳብ ነው፡፡
7. ጲላጦስ ኢየሱስን ቢፈታ የቄሳር ወዳጅ እንዳልሆነ የተናገሩት ሃሳብ ነው፡፡ ከቄሳር ጋራ ወዳጅ መሆን ለጲላጦስ ከማንኛውም ነገር የሚበልጥ አድርጎ ስለሚመለከተውና ወዳጅነቱን ለማቆየት ምንም ነገር ለማድረግ እንደማይመለስ ስለሚያውቁ ነው አይሁድ ይህንን ወጥመድ የተጠቀሙት፡፡
8. በዚህ ስፍራ አይሁድ ሲወስዱ የሚታዩት ጥንቃቄ ፋሲካን ለመብላት ዝግጅት ላይ ስለነበሩ ላለመርከስ ሲሞክሩ ነው፡፡ ለጲላጦስ ጥያቄ የመለሱት ኢየሱስ ወንጀለኛ እንደሆነና ይህ ባይሆን ኖሮ ወደ እርሱ ፊት እንደማያቀርቡት በማረጋገጥ ነው የነገሩት፡፡

# ጥናት አርባ አንድ ዮሐንስ 19፡17-42 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በሁለቱ ወገኖች መሃል አከራካሪ የነበረው ነገር፤ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉስ ነው ወይስ እርሱ ራሱ ስለራሱ የተናገረው ነገር ብቻ ነው በሚለው ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ጲላጦስ ያሳየው የአቋም ጥንካሬ ከበፊቱ ለየት ያለ ነው፤ ከዚህ በፊት እነሱ ወዳመዘኑበት የሚሄድና በእነርሱ ሃሳብ የሚወሰድ ሰው እንደነበረ ስናይ፤ እዚህ ቦታ ግን የራሱ የሆነ ጠንካራ አቋም ሲወስድ ይታያል፡፡
2. በዚህ ክፍል የምናያቸው አራት ወታደሮችን ነው፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ እያለ ወታደሮቹ ያደርጉት የነበረው ነገር የእርሱን ልብስ መከፋፈል ነው፡፡ በሰው አመለካከት እጀ ጠባቡ በእጣ የሆነበት ምክንያት አንድ ወጥ ስለሆነና ለመቅደድ ስላልፈለጉ ሲሆን፤ ከእግዚአብሄር አንጻር ግን የመጽሃፍ ቃል እንዲፈጸም ነው፡፡
3. በዚህ ስፍራ የምናያቸው ሰዎች ኢየሱስ፣ የኢየሱስ እናት ማርያም፣ የማርያም እህት፣ የቀለዮጳ ሚስት ማርያም፣ መግደላዊት ማርያም፣ ኢየሱስ የሚወደው ደቀ መዝሙር ናቸው፡፡ ሶስት ማርያሞችን እናያለን፡፡ ይህ ክፍል የሚያረጋግጥልን ኢየሱስ ለእናቱ ግድ እንደሚለው፣ እንደሚወዳትና ከሞተ በኋላም እንዳትቸገር እንደሚያስብላት ያሳየናል፡፡
4. ወታደሮቹ ትንቢቱን ሲፈጽሙ ሳያውቁትና ሳይረዱት ሲሆን፤ ኢየሱስ ግን ትንቢቱን ሲፈጽም አባቱ የሰጠውን ሥራ (ዮሐ 17፡4) እንደሚፈጽም እያወቀ የሚያደርገው መሆኑ ልዩነታቸውን ያሳየናል፡፡ ኢየሱስ ‹‹ተፈጸመ›› ሲል ለሰዎች ልጆች ደህንነት የሚያስፈልገው ማናቸውም ነገር ሁሉ ተሰርቶ እንዳለቀ፤ እግዚአብሄር አብ የሰጠውም ተልዕኮ እስከመጨረሻው እንደተከናወነ የሚያመለክት ሃሳብ ነው፡፡
5. አይሁድ ጲላጦስን የለመኑት ነገር የተሰቀሉት ሰዎች ኢየሱስንም ጨምሮ ጭናቸው ተሰብሮ በድናቸው እንዲወርድ ሲሆን፤ ይህንን ያደረጉበትም ምክንያት የሰዎቹ ሬሳ በሰንበት ቀን በመስቀል ላይ እንዳይውል ነበረ፡፡ ጌታ ትንኝን አጥርቶ ግመልን መዋጥ ሲል በእግዚአብሄር ፊት ዋነኛ የሆነው ላይ ማተኮር ትቶ በጥቃቅን ነገር ላይ ትኩረት መስጠትን ሲሆን እነዚህም ሰዎች የሰው ህይወት ማጥፋታቸው ሳይታያቸው ሰንበትን መጠበቃቸው ዋና ማድረጋቸው፤ ትንኝ አጥርቶ ግመል መዋጥ እንደሆነ አየዋለሁ፡፡
6. ከሁለቱ ሰዎች የተለየ በኢየሱስ ላይ የተደረገው ነገር፤ ጎኑን በጦር መወጋት ነው፡፡ መከራው በዝርዝር የሰፈረልን ምክንያት በእርሱ እንድናምን ነው፡፡ በዚህ ወታደር የተፈጸሙት ሁለት ትንቢቶች፤ አንደኛው በመዝ 34፡20 የተነገረው ከአጥንቱ አንድም እንደማይሰበር ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በዘካ 12፡10 ላይ የወጉት እንደሚያዩት የተነገረው ትንቢት ናቸው፡፡
7. በኢየሱስ ቀብር ላይ ተሳታፊዎች ሆነው የምናያቸው ሰዎች የአርማትያሱ ዮሴፍና፣ ኒቆዲሞስ ናቸው፡፡ ዮሴፍ የአይሁድ ሸንጎ አባል፣ ጻድቅ ሰው፣ በሸንጎው ምክርና ድርጊት አልተባበረም፣ የአርማትያስ ሰው ነው፣ የእግዚአብሄርን መንግስት መምጣት ይጠባበቅ ነበረ፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች ኢየሱስን የተከተሉበት መንገድ ሰው በማያያቸውና በስውር እንደሆነ እናያለን፡፡ (ዮሐ 3፡1-2 ዮሐ 19፡38)
8. እነዚህ ክፍሎች የሚያረጋግጡልን የኢየሱስ ሞት ሰዎች የጠነሰሱትና ጲላጦስም ስልጣኑን የተጠቀመ ይምሰል እንጂ፤ እግዚአብሄር ራሱ ከዘላለም የወሰነው ነገር እንደሆነ እንረዳለን፡፡

## ጥናት አርባ ሁለት ዮሐንስ 20፥1-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ማርያም ወደ መቃብሩ የሄደችው በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን፣ በማለዳና ገና ጨለማ እያለ ነው፡፡ ይህንን እንድታደርግ የገፋፋት ኢየሱስ ላደረገላት ነገር ውስጧ የሞላው ፍቅር ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ማርያም ያደረገችው ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደነበረው ደቀመዝሙር መሄድና ሁኔታውን መንገር ነበረ፡፡ የሰጠቻቸው መረጃ ኢየሱስን ሰዎች እንደወሰዱት ሲሆን ይህ ትክክለኛነት የጎደለው መረጃ ነበረ፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ከመቃብር የተነሳ እንጂ የተሰረቀ ስላልነበረ ነው፡፡
2. ጴጥሮስ ከሌላኛው ደቀመዝሙር የተለየ የተመለከተው ነገር በኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውን ጨርቅ ነው ያየው፡፡ ዮሐንስ በፍጥነት በመሮጥና ቀድሞ ወደ መቃብሩ በመድረስ ሲበልጠው፤ ጴጥሮስ ደግሞ ደፍሮ አስቀድሞ ወደ መቃብሩ ውስጥ በመግባት በልጦታል፡፡
3. ወደ መቃብሩ ውስጥ ገብቶ ሁኔታውን መመልከቱ የኢየሱስን ከሙታን መነሳት እንዳረጋገጠለትና እንዲያምን እንደረዳው እናያለን፡፡ ደቀመዛሙርቱ ከሙታን ስለመነሳቱ ያስተማራቸውንም ሆነ በመጽሐፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን ነገር ገና እንዳልገባቸው ይነግረናል፡፡
4. በነበረችበት ስፍራ በመቆየቷ ሁለቱን መላዕክት አየች፣ ከሞት የተነሳውን ኢየሱስን አየች፣ አነጋገረች፣ ከዚህም በላይ ደግሞ ለደቀ መዛሙርቱ የሚሆን መልዕክት ከኢየሱስ ተቀበለች፡፡ ሁለቱ ጥያቄዎች ‹‹ለምን ታለቅሻለሽ?›› የሚልና ‹‹ማንን ትፈልጊአለሽ?››
5. በዚህ ክፍል የማየው ተአምራት በር ተቆልፎ እያለ ኢየሱስ ሳይከፈትለት ገብቶ በመሃላቸው መገኘት መቻሉ ነው፡፡ በኢየሱስ መገኘት የተሰማቸው ነገር የደስታ ስሜት ነው፡፡ ደቀመዛሙርቱ በኢየሱስ መገኘት ደስ የተሰኙበት የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም፤ አንደኛው ግን አይሁድን ፈርተው የተሰበሰቡ በመሆኑ በኢየሱስ ከሞት መነሳት አንገታቸውን ቀና አርገው መሄድ ስለሚችሉ ነው፡፡
6. በመጀመሪያ ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› ብሎ የተወጉትን እጆቹንና ጎኑን አሳያቸው፡፡ በሁለተኛው ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› ብሎ ደግሞ ተልዕ እንደሰጣቸውና መንፈሱን እፍ እንዳለባቸው እናነባለን፡፡ የመጀመሪያው በሞቱ ከአባቱ ጋራ እንዳስታረቃቸውና ሰላም እንደፈጠረ ያረጋገጠበት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የውስጥ ሰላም የሞላቻቸው ሰዎች እንደሆኑና የእግዚአብሄር ሰላም ዘሪዎች እንደሆኑ ያረጋገጠበት ነው እላለሁ፡፡
7. አያሌ የሆኑትን ታምራዊ ምልክቶች አላሰፈረልንም፡፡ ዮሐንስ የጻፈበት ዋነኛ ዓላማ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ አምነን በስሙ ህይወት ይሆንልን ዘንድ ነው፡፡
8. ቶማስ ከደቀመዛሙርት ጋራ ባለመገኘቱ ያመለጠው ነገር የኢየሱስን የመገኘቱ በረከት ሲሆን፤ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ የሚታየው ከወገኖቹ ጋራ መገኘቱ የኢየሱስነ መገኘት መለማመድ እንደቻለ እናያለን፡፡ አንተስ በቅዱሳን ጉባኤ መገኘት አስፈላጊነቱን ምን ያህል ተረድተሃል? በቅዱሳን ጉባኤ መገኘታችን በመዝ 133፥1-3 እንደተነገረው የጌታን መገኘት የምንለማመድበት ቦታ መሆኑን አንዘንጋ፡፡

# ጥናት አርባ ሶስት ዮሐንስ 21፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በመሪነት ደረጃ የምናየው ጴጥሮስን ሲሆን የነበሩት ተከታዮችም ቁጥር ከራሱ ጋራ ስድስት ነበሩ፡፡ ምንም ችሎታውና እውቀቱ ቢኖራቸው ያለ ኢየሱስ ምንም ማድረግ እንደማይቻል መማር ይችላሉ፡፡ ለእኛም በእውቀታችንና በማስተዋላችን ሳንመካ በእርሱ መታመን እንደሚኖርብን መማር እንችላለን፡፡
2. ኢየሱስ ያዘዛቸው ትዕዛዝ መረባቸውን ከጀልባው ወደ ቀኝ እንዲጥሉ ነው፡፡ የማያውቁትን ሰው ትዕዛዝ ለመስማትና ለመታዘዝ ክፍት የሆኑበት ምክንያት እኔ እንደሚመስለኝ ቢሰሙትና ቢያደርጉት የሚጎድልባቸው ነገር ስለሌለ፤ እንደተባለው ከሆነ ግን ማትረፊያ እንደሚሆንላቸው በማሰብ ተስፋ በቆረጠ መንገድ ያደረጉት ይመስለኛል፡፡
3. በሉቃስ 5፡4-11 ኢየሱስ ይህንኑ የመሰለ ተመሳሳይ ተአምር ያሳያቸው በመሆኑና ያንን በማስታወስ ይመስለኛል ወደዚህ አነጋገር የደረሰው፡፡ አሳ የሚያጠምዱበት መረብ ምንም ያህል አሳ ቢይዝ አለመቀደዱ፤ በእኛም አገልግሎት ወንጌላችን ምንም ያህል ነፍሳትን ብንይዝበት የማይደክምና ሃይሉ የማይከሽፍ ብርቱ መሳሪያ መሆኑን መማር እንችላለን፡፡
4. ኢየሱስ በዚህ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ የተናገራቸው አንድ ነገር ‹‹ኑ ቁርስ ብሉ›› የሚል ነበረ፡፡ ይህንን ካላቸው በኋላ ጌታ ያደረገው ነገር እንጀራውንና አሳውን እንዲመገቡ ሲሰጣቸው እንመለከታለን፡፡ እነዚህን የዛሉና የደከሙ ደቀመዛሙርት መግቦ ያበረታ ጌታ እኔም በመንፈሴ ስደክምና ስዝል እንደሚመግበኝና እንደሚያበረታኝ ተስፋ ሆኖልኛል፡፡
5. የኢየሱስ ጥያቄዎችና የጴጥሮስም መለሰሶች ያተኮሩት በፍቅር ላይ ሲሆን፤ ከጴጥሮስ መልስ አስከትሎ ኢየሱስ የተናገራቸው ሃሳቦችም ትኩረታቸው ሃላፊነትን የተመለከቱ ነበሩ፡፡ እግዚአብሄር ሃላፊነት ሲሰጥ ለእርሱ ካለን ፍቅር ተነስተን እንድናገለግለው እንጂ ግዴታን ከመወጣት ተነስተን የምናደርገው እንዳይሆን የሚያስተምረን ነው፡፡
6. እነዚህ ሁለት ክፍሎች የሚመሳሰሉትና የሚያስተምሩን አንድ እውነት ቢኖር  እግዚአብሄርን ለማክበር አማኝ በህይወቱ ብቻ ሳይሆን በሞቱም እግዚአብሄርን ማክበር እንደሚችል ከሁለቱም ጥቅሶች መማር እንችላለን፡፡
7. ይህ አይነቱ ወሬ የተነሳው ኢየሱስ ለጴጥሮስ ጥያቄ ከሰጠው መልስ ነው፡፡ ይህ ችግር በቤተክርስትያን አካባቢም በብዙ የሚታይና ብዙ ችግር የሚፈጥር ነው፤ ለዚህም መፍትሄ የሚሆን የሚመስለኝ ነገሩ ካልገባን የተናገረውን ሰው ይህንን ስትል ምን ማለትህ ነው ብለን ብንጠይቅ እውነቱን መረዳት እንችላለን፡፡
8. ጴጥሮስ በተጨማሪ ማወቅ የፈለገው ነገር የዮሐንስ መጨረሻ ምን እንደሚሆን ማወቅ ነበረ፡፡